# ፍራንሲስ ሀውል ት/ቤት ዲስትሪክት

## የተማሪ ሥነ-ምግባር ደንብ

Francis Howell
SCHOOL DISTRICT

HOME SCHOOL COMMUNITY

LEARNING TOGETHER

# የይዘት ማውጫ ሰንጠርዥ


**መግቢያ** ........ 3

**የመማሪያ ክፍል ስነ-ስርዓት መመሪያዎች** ........ 4

**የባህሪ ግድፈቶች (ጥሰቶች) እና ተዛማጅ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች** ........ 5

**የባህሪ ግድፈቶች እና ተዛማጅ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች** ........ 6

**የዲሲፕሊን ትርጓሜዎች** ........ 16

**የተማሪዎች የአልኮል እና የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ አጠቃቀም** ........ 18

**ከጠመንጃ-ነፃ ትምህርት ቤቶች** ........ 19

**የአውታረ-መረብ እና የበይነ-መረብ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም መመሪያዎች** ........ 20

**አካላዊ ቅጣት ክልክል ነው** ........ 21

**የአውቶቡስ መመሪያዎች** ........ 22

**የቃላት መፍቻ** ........ 22

# መግቢያ

**አዎንታዊ የሆኑ፣ መከባበር የሰፈነባቸው የትምህርት ቤት አካባቢዎች ለመማር ወሳኝ ናቸው**

ሁሉም ሰው ትምህርት ቤቱ እንግዳ ተቀባይ፣ ሰላማዊ እና መከባበር የሰፈነበት ቦታ እንዲሆን ይፈልጋል። ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ሰራተኞች እና ማህበረሰቡ በጋራ አብረው በመስራት፣ ትምህርት ቤታቸውን ለመማር በጣም አመቺ የሆነ ቦታ ማድረግ ይችላሉ። ርዕሰ መምህሩ አዎንታዊ የመማር ማስተማር አካባቢን ጠብቆ የማቆየት ኃላፊነት አለበት። ተማሪች የሚከተሉትን በማስታወስ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ማበርት ይችላሉ፡-

- የራስን እና የሌሎችን ደኅንነት ጠብቅ/ቂ፣ በኃላፊነት ተንቀሳቀስ/ሽ እና ረጋ በል/ይ
- ሁሉንም የዕድሜ እኩዮችህ.ሽ እና አዋቂዎች አክብር/ሪ
- ሁሉንም የትምህርት ቤት ንብረት በጥንቃቄ እና በአግባቡ ያዝ/ዢ
- ትምህርት ቤት እና የመማሪያ ክፍሎችህ/ሽ ውስጥ በሰዓቱ ተገኝ/ኚ
- ለትምህርት ክፍሎች ዝግጁ ሁን/ኚ፣ ይህም የቤት ስራ መስራትን እና የትምህርት ቁሳቁስ ይዞ መገኘትን ያካትታል
- በትምህርትህ ላይ በንቃት ተሳተፍ/ፊ
- መልካም/ደግ ሁን/ኚ እና ተገቢ የሆነ ቋንቋ ብቻ ተጠቀም/ሚ
- ልብስ በአግባቡ ልበስ/ሺ
- የትምህርት ቤቱን ህግጋት እና የመምህራኖችህን/ሽን መመሪያ ተከተል/ይ
- ከሌሎች ጋር ያሉክ/ሽ ልዩነቶችን አክብር/ሪ እና ተቀበል/ዪ
- ምን ዓይነት ስሜት እየተሰማቸው እንደሆነ ወይም ምን እንደሚፈልጉ ኢጋዥ እና ተገቢ በሆነ መንገድ ብቻ ግለጽ/ጪ
- አለመግባባቶችን ተቀባይነት ባላቸው መንገዶች ብቻ ፍታ/ቺ

**የባህሪ ድጋፍ**

አብዛኞቹ የ FHSD ትምህርት ቤቶች ተፈላጊ የሆኑ ባህሪዎችን ለማስተማር እና ተጨማሪ ማጎልበቻ/ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን ለማገዝ ባለ ብዙ ደረጃ (Multi-Tiered) የድጋፍ መስጫ ስርዓት አቀራረብን ተግበራዊ አድርገዋል።

**የስነ-ምግባር ትምህርት**

አብዛኞቹ የ FHSD ትምህርት ቤቶች በአእምሮ፣ በማህበራዊ ግንኙነት እንዲሁም በግብረ-ገብ ላይ በመስራት የወጣቶች አዎንታዊ የስነ-ምግባር ባህሪያትን በማዳበር "ተንከባካቢ የተማሪዎች ማህበረሰብ" ለመፍጠር የሚሰራ በአግባቡ የተዘጋጀ የስነ-ምግባር ትምህርት ፕሮግራሞችም አሏቸው። ዲስትሪክቱ የሚዙሪ በሥነ-ምግባር የታነፀ ትምህርት ቤት ስያሜን የተቀበሉ (3) ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ብሔራዊ የስነ-ምግባር ትምህርት ቤት እውቅና የተሰጣቸው (2) ትምህርት ቤቶች አሉት።

**በውስጤ ያለ መሪ**

አንድ የ FHSD ትምህርት ቤት የተማሪዎች የአመራር ብቃትን ለማሳደግ እንደሚያስችል አንድ መንገድ የኮቪይ በውስጤ ያለ መሪ (Covey's Leader In Me) የተሰኘ ፕሮግራምን ተግበራዊ አድርጓል። *የከፍተኛ ስኬታማ ሰዎች 7ቱ ልማዶችን (The 7 Habits of Highly Effective People) መሰረት በማድረግ፣* በውስጤ ያለ መሪ ፕሮግራም ተማሪዎች በ 21ኛው ክፍለ-ዘመን ኢኮኖሚ ውስጥ ስኬታማ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልጓቸው በራስ መተማመን እና ክህሎቶችን ያስታጥቃል። በውስጤ ያለ መሪ ፕሮግራምን ተግባራዊ የሚያደርጉ ትምህርት ቤቶች የተሻሻለ የትምህርት ቤት ባህል እና በአጠቃላይ የቀነሱ የዲስፕሊን ችግሮችን በቋሚነት ሪፖርት ደርጋሉ።

የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ተብሎ የሚታሰብ የተማሪ ባህሪ ምን ዓይነት እንደሆነ ይገልፃል። እንደዚህ ዓይነት ባህሪን ለመከላከል ሊያገለግሉ የሚችሉ የተለያዩ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን እና ተማሪዎች የተገለፀውን ባህሪ ሲያሳዩ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ የቅጣት እርምጃዎችንም ያቀርባል። የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ለተማሪዎች መመሪያ፣ እቅጣጫ፣ እና ድጋፍን በመስጠት በትምህርት ቤት ስኬታማ መሆን የሚያስችሉ ጣልቃ ገባዊ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ጥቅም ላይ ማዋልንም ይደግፋል።

# የመማሪያ ክፍል ስነ-ስርዓት መመሪያዎች

ከተማሪዎች ጋር አዎንታዊ የሆኑ ግንኙነቶችን መገንባት ስኬታማ ለሆነ የትምህርት ክፍል አስተዳደር የማዕዘን ድንጋይ ነው። መምህራን ለመማር ማስተማር ተስማሚ የሆነ የመማሪያ ክፍልን የመፍጠር እና ይህንንም ጠብቆ የማቆየት ኃላፊነት አለባቸው። በማህበረሰብ አባላት መካከል የሚደረጉ የተዋቀሩ የቡድን ውይይቶች/ስብሰባዎች (Community-building circles) እራሱን በእራሱ የሚመራ እና የሚቆጣጠር ግድ የሚለው ማህበረሰብ ለመፍጠር እንደሚያስችል አንድ መንገድ ተግባራዊ እንዲደረግ በዲስትሪክቱ ይበረታታል። በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ጠንካራ፣ አዎንታዊ ግንኙነቶች ያሏቸው የመማሪያ ክፍሎች አሳታፊ ውጤታማ የትምህርት አካባቢዎችን ለመፍጠር እና ለማስቀጠል አስተዋፅዖ ያበረክታሉ። ተማሪዎች እርስ በእርሳቸው የሚተባበሩበት እና ለህብረተሰቡ ብሎም ለስራ ቅጥር ዝግጁ የሚያደርጓቸው ክህሎቶች ማዳበር በሚችሉበት የትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ ቢማሩ የተሻለ ይሆናል ብለን እናምናለን። ከልክ ያለፈ ወሬ፣ ከመቀመጫ ውጭ መገኘት፣ ቁሳቁሶችን መወርወር፣ ሌሎችን መረበሽ፣ ተገቢ ያልሆነ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ ፅሑፍ ያለባቸው ወረቀቶችን መቀባበል እና/ወይም ሌሎች የትምህርት ሂደቱ ላይ ጣልቃ የሚገቡ ተግባራትን የሚያጠቃልል ነገርግን በነዚህ ብቻ ያልተገደበ፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚፈጠር ረብሻ ወይም የረብሻዎች ጥምረት ተቀባይነት የለውም።

## የዲሲፒሊን እርምጃ ደረጃዎች

| የዲሲፕሊን ችግር | እርምጃ |
|---|---|
| መጀመሪያ ለሚፈጠር ችግር | መምህሩ ከተማሪው ጋር ይነጋገራል/ይመካከራል |
| ችግሩ ሲቀጥል | መምህሩ ለተማሪው ማስጠንቀቂያ ይሰጣል<br>አስተማሪው ተማሪውን ወደ ስሜት መቆጣጠሪያ፣ እረፍት መውሰጃ ወይም መረጋጊያ ክፍል ሊልከው ይችላል<br>መምህሩ ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች)ን ሊያገኝ ይችላል |
| ከማስጠንቀቂያ በኋላ ችግሩ ካልተፈታ | መምህሩ ተማሪው በዲቴንሽን (detention) ጊዜ እንዲያሳልፍ ወይም ከተማሪው እና/ወይም ከወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ጋር በጋራ ችግር ለመፍታት የሚያስችል ስብሰባ ማካሄድን ሊመርጥ ይችላል |
| ከዲቴንሽን (detention) ወይም ከስብሰባው በኋላም ችግሩ ካልተፈታ | መምህሩ ተማሪውን ርዕሰ መምህሩ ቢሮ እንዲሄድ ያደርገዋል |

## መዘግየት ላይ የምንከተለው ፖሊሲ

ተማሪዎች ደወል ከተደወለ በኋላ ወደ መማሪያ ክፍል ሲደርሱ በመምህሩ/በርዕሰ መምህሩ የዲቴንሽን (detention) እርምጃ ሊተላለፍባቸው ይችላል። ምን ያህሉ የመዘግየት አጋጣሚዎች ወደ ዲቴንሽን (detention) እንደሚያመሩ በእያንዳንዱ የተናጠል ትምህርት ቤት ሕንፃ አስተዳደር ይወሰናል። ብዙ መዘግየቶች ከተጠራቀሙ በኋላ፣ ተማሪዎች ለተጨማሪ የዲሲፒሊን እርምጃ ወደ ቢሮ ሊላኩም ይችላሉ።

# የባህሪ ግድፈቶች (ጥሰቶች) እና ተዛማጅ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች

የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ፖሊሲዎች ለደህንነት፣ ክዋኔ እና ግላዊ ስኬት ቅድሚያ የሚሰጥ አዎንታዊ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እና ጠብቆ ለማቆየት እንዲያስችሉ ተደርገው የተነደፉ ናቸው። ስለዚህ፣ ቀጣይ ባሉ ገፆች ላይ የቀረቡት ገበታዎች (charts) በፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የተገለፁ የባህሪ ግድፈቶች (ጥሰቶች) እና ተዛማጅ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃን ያሳያሉ።

ለአንደኛ ደረጃ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚወሰዱ የዲስፕሊን እርምጃ ደረጃዎች ሊለያዩ ይችላሉ። የዲሲፒሊን እርምጃው ዋነኛ ዓላማ ተቀባይነት ያለው፣ ተገቢ ባህሪ ለማስተማር እና ተገቢ ያልሆነ ባህሪ ለወደፊት እንዳከሰት ለመከላከል መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

በቀጣይ ገፆች ላይ የተዘረዘሩት የባህሪ ግድፈቶች (ጥሰቶች) እና ተጓዳኝ መዘዞች ለሁሉም ተማሪዎች ለድሜያቸው ተገቢ በሆነ መልኩ እንዲብራራላቸው ይደረጋል። ወላጆች የተዘረዘሩት የባህሪ ግድፈቶችን (ጥሰቶችን) እና ተጓዳኝ መዘዞችን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲከልሱ ይበረታታሉ።

በትምህርት ቤት የሚዘጋጁ ትምህርታዊ ጉዞዎች ወይም ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውጭ የሚከናወኑትን ጨምሮ ሌሎች በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ ተግባራት ኃላፊነት እንዲወስዱ በይፋ በተሰየሙ የት/ቤት ሰራተኞች ክትትል እና ቁጥጥር ስር ሆነው ይከናወናሉ። ለአንደኛ ደረጃም ሆነ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች (ለመካከለኛ እና ከፍተኛ ት/ቤት ተማሪዎች) በነዚህ ተግባራት ወቅት ሁሉም የዲስትሪክቱ መመሪያዎች እና ደንቦች ተግባራዊ ይሆናሉ። ተማሪዎች በመስክ ትምህርታዊ ጉዞዎች እና ከ FHSD ንብረት ውጭ በሚካሄዱ ተግባራት ወቅት ለሚከሰቱ የስነምግባር ግድፈቶች (ጥሰቶች) በተማሪ ሥነ-ምግባር ህግ መሰረት ተጠያቂ ይደረጋሉ።

ከት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጭ የሚከሰቱ አጋጣሚዎች ከትምህርት ቤት ጋር ትስስር (ግንኙነት) ካላቸው ወይም አጋጣሚዎቹ በትምህርት ቤቱ ከባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ካስከተለ FHSD የተማሪ ስነምግባር እርምጃዎችን የመወሰን ስልጣን አለው፣ ይወስናልም።

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ እያንዳንዱን እና ሁሉንም የእርምት እርምጃ መውሰድ የሚጠይቁ የጥፋት ዓይነቶችን እንዲዘረዝር ወይም እንዲገልፅ አይጠበቅበትም። ምንም እንኳን አጠቃላይ መመሪያዎች ቢኖሩም፣ ድስትሪክቱ በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ በመመስረት በተለይ በጉዳዩ ስር ባለው የባህሪይ ግድፈት ተፈጥሮ፣ ከባድነት እና ድግግሞሽ ላይ ተመስርቶ ለተፈጠረው ሁኔታ ተገቢ ሊሆን የሚችል የትኛውንም ተስማሚ የሆነ ውሳኔን የመወሰን/የመምረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

## የባህሪ ግድፈቶች እና ተዛማጅ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎች

**የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ 1፡-** የክፍል ውስጥ ጣልቃ ገብነቶች ከዲሲፕሊን እርምጃ ጋር ወይም ያለ ዲስፕሊን እርምጃ

- መምህሩ ከተማሪው ጋር ይወያያል እንዲሁም ተገቢ የሆነ ባህሪ እና የመማሪያ ክፍል ደንቦችን በተመለከተ እንደገና ትምህርት ይሰጣል
- ተማሪው ወደ ስሜት መቆጣጠሪያ፣ እረፍት መውሰጃ ወይም መረጋጊያ ክፍል ይልከዋል
- ከባህሪው ጋር በተገናኘ ለወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) የቃል/የፅሁፍ መልዕክት ይልካል
- እንደ ማበረታቻዎች ወይም ከስርአተ ትምህርቱ ባሻገር ያሉ ሌሎች ልዩ መብቶችን መከልከል
- የመምህር/ወላጅ/አሳዳጊ ኮንፈረንስ
- የእረፍት ጊዜዎችን መከልከል - በከፊል/ሙሉ በሙሉ (የባህሪ ግድፈቶችን (ጥሰቶችን) ለመፍታት ሌሎች አማራጮች ከሌሉ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላሉ።)
- ዲቴንሽን (Detention)
- ወደነበረበት መመለሻ ጉባኤ (Restorative Conference)

**የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ 2፡-** የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጣልቃ ገብነቶች ከዲሲፕሊን ወይም ያለ ዲስፕሊን እርምጃ

- ደረጃ 1 ምላሾች እና/ወይም ወደነበረበት መመለስ
- 1ኛ ጥፋት - እስከ 3 ቀናት በሚደርስ ዲቴንሽን ከመደበኛ ክፍል ውጪ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል
- 2ኛ ጥፋት - እስከ 5 ቀናት ከመደበኛ ክፍል ውጪ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል
- 3ኛ እና ከዚያ በኋላ ለሚከሰቱ ተከታታይ ጥፋቶች - እስከ 5 ቀናት ከት/ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል
- ወደነበረበት መመለሻ ጉባኤ (Restorative Conference)

**የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ 3፡-** ጠናከራ ጣልቃገብነት እና አስተዳደራዊ የዲሲፕሊን እርምጃ (ተግሣጽ)

- ደረጃ 1-2 ምላሾች እና/ወይም
- የበርካታ ቀናት ከመደበኛ ክፍል ውጪ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል እና/ወይም እስከ 10 ቀናት ከት/ቤት ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል (በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ ጥምር እገዳ መጣልን መጠቀም የሚቻል ቢሆንም ከ 10 ቀናት ግን መብለጥ የለበትም)
- ወደነበረበት መመለሻ ጉባኤ (Restorative Conference)

**የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ 4፡-** ጠናከራ ስልቶች፣ ጣልቃገብነት እና አስተዳደራዊ የዲሲፕሊን እርምጃ (ተግሣጽ)

- እስከ 10 ቀናት ለሚደርስ ጊዜ ከት/ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል እና ጉዳዩን ወደ ስነ ምግባር ችሎት ኮሚቴ በመላክ/በማስተላለፍ እስከ 180 ቀናት ሊደርስ የሚችል ተጨማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣልን ሊያስከትል ይችላል
- ወደነበረበት መመለሻ ጉባኤ (Restorative Conference)

**የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ 5፡-** ከትምህርት ቤት ለረጅም ጊዜ መባረርን እና እንደገና ወደ ትምህርት የመመለስ ስልቶችን ያካተተ ጠንካራ ጣልቃገብነት

- ለ 10 ቀናት ከት/ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል እና ጉዳዩን ወደ ስነ ምግባር ችሎት ኮሚቴ በመላክ/በማስተላለፍ እስከ 180 ቀናት ሊደርስ የሚችል ተጨማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣልን ሊያስከትል ይችላል
- በቋሚነት ለማባረር የሚያስችል ምክረ ሀሳብ
- የጦር መሳሪያን ያካተተ የስነምግባር ጥሰት - ተማሪው ቢያንስ ከአንድ ዓመት (ከ 365 ካላንደር ቀናት) ላላነሰ ጊዜ ከትምህርት ቤት ይታገዳል ወይም በቋሚነት ይባረራል ይህም በሚዙሪ ህግ ክፍል Rev. § 160.261 መሰረት የሚወሰን ይሆናል

* (Elem) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃዎችን ይጠቁማል
* የስነምግባር ግድፈቶች (ጥሰቶች) ደረጃ ሲወሰን ዓላማ፣ የተፅዕኖ ወሰን እና የባህሪው ክብደት ከግምት ውስጥ ይገባል።

## ዘለፋዊ/ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ/ፀያፍ ስድብ (AL)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| መራገም፣ መሳደብ፣ ወይም የብልግና ምልክቶችን ማሳየት፣ ወይም በጽሁፍ ሆነ በቃላት የተገለጹ ነገር ግን በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ያላነጣጠሩ አሉታዊ ወይም አዋራጅ አስተያየቶች ወይም አገላለፆች። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| መራገም፣ መሳደብ፣ ወይም የብልግና ምልክቶችን ማሳየት፣ ወይም በጽሁፍ ሆነ በቃላት የተገለጹ ነገር በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ያነጣጠሩ አሉታዊ ወይም አዋራጅ አስተያየቶች ወይም አገላለፆች። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| በትምህርት አካባቢ ተገቢ ያልሆነ ወይም የክፍል ስራን፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም የትምህርት ቤት ተግባራትን ጉልህ በሆነ መልኩ የሚረብሽ የጥላቻ ንግግርን ጨምሮ ጸያፍ፣ ስድ፣ ተገዳዳሪ የሆነ አጓጉል የቋንቋ አጠቃቀም ወይም የ። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |

## አልኮል (A)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| አልኮል ያለበት ማንኛውንም መጠጥ መያዝ፤ የአልኮል መጠጥ ከጠጡ በኃላ ብዙም ሳይቆዩ መጨመር እና/ወይም በተጽእኖው ስር መውደቅ፣ | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| አልኮል ያለበት መጠጥ ማሰራጨትት | | | | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ሆን ብሎ የእሳት ቃጠሎ ማስነሳት (AR)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሆን ብሎ እሳት ማያያዝ፣ ወይም እሳት ለማስነሳት መሞከር | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ጉዳት ያስከተለ ጥቃት (ANI)

ደረጃ 4 እና 5 ወደ መደበኛ የሕግ አስከባሪ አካላት ጉዳዩን መምራት/መላክን ይጠይቃሉ።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ተማሪ ወይም ሰራተኞችን ለመግደል ወይም ከባድ አካላዊ ጉዳት ለማድረስ ሙከራ ማድረግ—ከባድ አካላዊ ጉዳት ለማድረስ በማቀድ ተማሪ ላይ ኃይል መጠቀም። በትምህርት ቤት አስተዳደር ወደ ሕግ አስከባሪዎች ጉዳዩ ይተላለፋል | | | | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ጉዳት ያላስከተለ ጥቃት (AS)

ደረጃ 4 እና 5 ወደ መደበኛ የሕግ አስከባሪ አካላት ጉዳዩን መምራት/መላክን ይጠይቃሉ።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| መምታት፣ በጥፊ መምታት፣ መግፋት፣ ማደናቀፍ/ማሰናከል፣ በኃይል መግፋት፣ መራገጥ፣ መትፋት ወይም ጉልበተኝነትን ወይም ጥቃትን የማያካትትት እና ወደ ድብድብ እና አካላዊ ጥቃትን ደረጃ ያልደረሰ አንድ ተማሪ በሌላ ተማሪ ላይ ያሳየው ተገቢ ያልሆነ ጠብአጫሪ ባህሪ። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| በተማሪ ላይ የሚፈፀም አካላዊ ጥቃት | | | ■ ደረጃ 3 (Elem) | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| አካላዊ ኃይልን መጠቀም፣ ቁሳቁስን በመጠቀም ጭምር፣ በቀጥታ በትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ላይ ወይም በት/ቤት ውስጥ ወይም በማንኛውም የት/ቤት እንቅስቃሴ ላይ ህጋዊ ስልጣን በተሰጠው ማንኛውም አዋቂ ላይ በቀጥታ የተቃጣ ጥቃት ወይም ተጽእኖ። | | | | ■ ደረጃ 4 (Elem) | ■ ደረጃ 5 |

## ቦምብ/በትምህርት ቤት ውስጥ የተቃጣ ዛቻ/የሐሰት ማንቂያ (BT)

የዛቻውን ትክክለኛነት እና ክብደት ለማወቅ በተቃጣው ዛቻ ላይ ግምገማ ይካሄዳል።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የሐሰት ማንቂያ – የትምህርት ቤቱን የእሳት እና/ወይም ሌላ የማንቂያ ደወል ማስነሳት፣ የእሳት አደጋ ሳይነሳ እሳት ተነሳ ብሎ ሪፖርት ማድረግ ወይም ወደ 911 የሐሰት የማንቂያ ጥሪ ማድረግ | | ■ ደረጃ 2 (Elem) | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |
| ርችት፣ የጭስ ቦምብ፣ የሚረጭ /በጋዝ መልክ የተዘጋጀ በርበሬ (pepper spray/gas)፣ MACE፣ አስለቃሽ ጭስ ወይም የሚሰነፍጥ ሽታ የሚለቅ ቦምብ ለመጠቀም መሞከር ወይም መጠቀም | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |
| ሰዎችን ለማስፈራራት ወይም ለማወክ፣ የመማር ማስተማር ሒደቱን ለማወክ፣ ወይም የዲስትሪክቱን ንብረት ለቀው እንዲወጡ ወይም እንዲዘጋ ለማድረግ ለትምህርት ቤት ወይም ለበርካታ ሰዎች ማስፈራሪያ ወይም የውሸት ሪፖርት (በቃል፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በጽሁፍ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ) ማሰራጨት። ይህ የጦር መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የማምጣት ዛቻን ይጨምራል | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| በትክክል ቦምብ ወይም ፈንጂ ሳይያዙ ቦምብ ይገለሁ ብሎ ማስፈራራት ወይም ፈንጂ ለማፈንዳት መዛት/ማስፋራራት | | | | | ■ ደረጃ 5 |
| ቦምብ ወይም ሌላ የሚፈነዳ/ተቀጣጣይ ነገር ይዞ መገኘት | | | | | ■ ደረጃ 5 |

## ጉልበተኝነት/የሳይበር ጉልበተኝነት (BULLY)

አስፈላጊ ንዑስ ኮድ፡- BD – በአካል ጉዳት ላይ ተመሰርቶ የሚቃጣ ጉልበተኝነት፣ BR – በዘር/በብሔር ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ጉልበተኝነት፣ BS – በፆታ ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ጉልበተኝነት፣ BSO – በፆታዊ ዝንባሌ ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ጉልበተኝነት፣ BBR – በሐይማኖት ላይ ተመሰርቶ የሚቃጣ ጉልበተኝነት፣ B-OTH – በሌሎች የሚቃጣ ሌላ ማንኛውም ጉልበተኝነት

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በተደጋጋሚ የተፈፀመ ወይም እንደገና የመከሰት እድሉ ከፍተኛ የሆነ እንዲሁም ማንኛውም ተማሪን ለአካላዊ ደኅንነቱ ወይም ለንብረቱ እንዲሰጋ የሚያደርግ (በሰላማዊ ትምህርት ቤት ህግ ስር የወንጀል ትንኮሳ ተብሎ የተጠቀሰውን ጨምሮ) ማስፈራራት/ዛቻ፣ ያልተፈለገ ጠብ አጫሪ ባህሪ ወይም ትንኮሳ፤ እንደገና የመከሰት እድሉ ከፍተኛ የሆነ እና ማንኛውም ተማሪን ለአካላዊ ደኅንነቱ ወይም ለንብረቱ እንዲሰጋ የሚያደርግ፤ በማንኛውንም ተማሪ ትምህርታዊ አፈፃፀም፣ እድሎች ወይም ጥቅሞች ላይ ያለምንም ልዩነት ጣልቃ የሚገባ፤ ወይም የመማር ማስተማር ሂደቱን በእጅጉ የሚያስተጓጉል፤ ጉልበተኝነት የሰውነት እንቅስቃሴን/አካላዊ ምልክቶችን፣ ወይም በቃል የሚተላለፉ መልእክቶችን፣ በሳይበር የሚቃጣ ጉልበተኝነትን፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በፅሁፍ የሚተላለፍ መልዕክትን እንዲሁም ይህን ተግባር ሪፖርት አደርጋለው በሚል ሰው ላይ የሚቃጣ የትኛውንም የበቀል ዛቻን ጨምሮ የሚፈፀሙ ተግባራትን ሊያጠቃልል ይችላል። “የሳይበር ጉልበተኝነት” ማለት በስልክ፣ በገመድ አልባ ስልክ ወይም በሌላ ገመድ አልባ የመገናኛ መሣሪያ፣ ኮምፒተር ወይም የሬዲዮ መገናኛን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ባልተወሰነ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ አማካኝነት መልእክት፣ ጽሑፍ፣ ድምጽ ወይም ምስልን ጨምሮ መረጃን ማስተላለፍ ማለት ነው። ተማሪዎች ህግ በሚፈቅድላቸው አግባብ ሀሳባቸውን በመግለጻቸው በትምህርት ቤቱ ሊቀጡ/የስነ ስርዓት እርምጃ ሊወሰድባቸው አይችልም | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ኮምፒዩተር/ቴክኖሎጂን አላግባብ መጠቀም (CTM)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በትምህርት ቀን፣ በዲስትሪክቱ ድጋፍ በሚቀርብ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መሳሪያውን መጠቀም የትምህርቱ አካል ካልሆነ በስተቀር፣ ወይም በሌላ መልኩ በህንፃው ርዕሰ መምህር ካልተፈቀደ በስተቀር የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን መጠቀም፣ ማሳየት ወይም ማብራት/መክፈት። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር ባደረገው ኩነት ላይ ፎቶግራፍ ነክ፣ የእይታ ምስሎችን መያዝ እና/ወይም ማሰራጨት ወይም የመማር ማስተማር ሂደቱን ማወክ/መስተጓጎል | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |
| ስኬታማ ሆነም አልሆነ ያልተፈቀደ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም መሞከር፤ ተገቢ ያልሆነ ይዘት መክፈት፤ ያለፈቃድ ከፍ ያለ ጥቅምን ማረጋገጥ፤ መጥለፍ፤ ማጣሪያ ዘዴዎችን ማምለጥ/ማሰናከል | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ማንጓጠጥ/ማዋረድ (DIS)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ቃላት፣ የድምፅ ቃና፣ በፊት ገፅታ፣ በፅሁፍ ወይም በሰውነት እንቅስቃሴ የሚተላለፉ መልዕክቶች | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |

## በጥባጭ/ረባሽ ባህሪ (DB)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በክፍል ውስጥ የሚከናወን የመማር ማስተማ ሂደትን እና የሌሎች ተማሪዎች ትምህርትን የሚረብሽ/የሚያውክ ባህሪ | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| የሚረብሽ፣ የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ውድመት የሚያስከትል እና/ወይም ከሌላ ተማሪ ወይም የእድሜ እኩያ ጋር አካላዊ ግንኙነት የሚፈጥር ቁስ (የበረዶ ኳስን ጨምሮ) በመጠቀም ሆን ብሎ መምታት፣ መወርወር ወይም መልቀቅ፣ ቁሱ የሚወረወረው ቁጥጥር የሚደረግበት ትምህርታዊ እንቅስቃሴ አካል ወይም ለታለመለት ዓላማ ሳይሆን ሲቀር። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |

## የልብስ አለባበስ ህግ ጥሰት (DCV)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የሚንሸራተት/ሰውነትን የሚያጋልጥ አለባበስ፣ የውስጥ አልባሳትን ማጋለጥ፣ ሹል ነገሮችን እና/ወይም ሰንሰለቶችን መልበስ፣ ወይም በጨርቆች/ጭምብሎች ላይ ተገቢ ያልሆኑ (ምሳ. ወሲባዊ ይዘቶችን፣ የአደንዛዥ ዕፆችን፣ አስካሪ መጠጦችን፣ የጦር መሳሪያዎች፣ ህገወጥ ተግባራትን ወዘተ.) የያዙ መልእክቶችን የሚያሳዩ ህትመቶችን የሚያካትት ነገርግን በነዚህ ብቻ ያለተገደበ የትምህርት ቤቱን የአለባበስ ህግ የሚጥስ፣ ለትምህርት ቤት ተግባራት ተገቢ ያልሆነ እና/ወይም ለመማር ማስተማር ሂደቱ አዋኪ የሆነ የአለባበስ ዘዬ። ርዕሰ መምህሮቹ ወላጆች ተገቢ የልብስ ቅያሪ ወደ ትምህርት ቤት ይዘው እንዲያመጡ ተማሪዎቹን ሊጠይቁ ይችላሉ። ተማሪው የትምህርት ቤቱን አለባበስ ኮድ የሚያሟላ ልብስ እንዲቀይር ከተጠየቀ በኋላ የአለባበስ ኮዱን እንደገና ጥሶ ከተገኘ ተጨማሪ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል። | ■<br>ደረጃ 1 | ■<br>ደረጃ 2 | | | |

## አደንዛዥ ዕፅ (D)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የካናቢስ ሽታ፣ ዕፁ ጥቅም ላይ መዋሉን የሚጠቁም ማስረጃ ባይኖርም ወይም በዕፁ ተፅዕኖ ስር መውደቅ ባይከሰትም፣ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ መስተጓጎልን ለመፍጠር በቂ ነው | | ■<br>ደረጃ 2 | | | |
| ካናቢስን ጨምሮ ማንኛውንም አደንዛዥ ዕፅ(ዎች)ን መጠቀም ወይም በማንኛውም አደንዛዥ ዕፅ ተጽእኖ ስር መውደቅ | | | ■<br>ደረጃ 3 | ■<br>ደረጃ 4 | ■<br>ደረጃ 5 |
| ካናቢስን ጨምሮ ማንኛውንም አደንዛዥ ዕፅ(ዎች)ን ወይም ከህገወጥ ወይም የተከለከለ ተግባራት ጋር የተገናኙ ቁሶችን ይዞ መገኘት | | | ■<br>ደረጃ 3 | ■<br>ደረጃ 4 | ■<br>ደረጃ 5 |
| ካናቢስ እና/ወይም ከካናቢስ ውጪ ያለ ሌላ ማንኛውንም አደንዛዥ ዕፅ(ዎች)ን መግዛት | | | | ■<br>ደረጃ 4 | ■<br>ደረጃ 5 |
| ካናቢስን ጨምሮ፣ ሌሎች አደንዛዥ ዕፅ(ዎች)ን፣ ለሌላ ተማሪ ማሰራጨት ወይም መጋራት | | | | ■<br>ደረጃ 4 | ■<br>ደረጃ 5 |
| በሐኪም ያልታዘዙ መድኃኒቶችን አካትቶ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ያልተወሰነ፣ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም የደረጃ 2 ጥፋት ነው። (በሐኪም ያልታዘዙ መድሃኒቶችን ጨምሮ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ያልተገደበ) ማሰራጨት፣ መሸጥ ወይም መሸመት ወይም “ያለ ሐኪም ማዘዣ በሚገዙ” መድሃኒቶች ጫና ስር በመውደቅ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚረብሹ ባህሪያትን መፈፀም ደረጃ 3 ጥፋት ነው። | | ■<br>ደረጃ 2 | ■<br>ደረጃ 3 | | |

## ማጋለጥ (EX)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ወሲባዊ ነክ ያልሆነ እንደ በአደባባይ መሽናት። | ■<br>ደረጃ 1<br>(Elem) | ■<br>ደረጃ 2 | ■<br>ደረጃ 3 | | |
| በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ መቀመጫን እና/ወይም ብልትን ማሳየትን ወይም የሌላን ሰው ወይም የራስን አልባሳት በማስወገድ/በማውለቅ ማንኛውንም ድብቅ የሰውነት ክፍሎችን/የብልትን እና/ወይም የውስጥ ልብሶችን ማጋለጥን ያጠቃልላል። “የሰው ሱሪ ማውለቅ” በዚህ ጥሰት ስር ይወድቃል። ይህ ወደ የሕንፃው ህግ አስከባሪ ሹም መላክን ሊያስከትል ይችላል በርዕሰ መምህሩ/ተወካዩ የጥሰቱ ክብደት በቂ ነው ተብሎ ከታመነ ደረጃ 3 ጥፋቶት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። | | ■<br>ደረጃ 2 | ■<br>ደረጃ 3 | | |

## መደባደብ (FG)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ለግጭቱ በንግግርም ሆነ በአካላዊ እንቅስቃሴ (ማለትም በመጎሸም፣ በመምታት፣ በእቃ መምታትንም ሊያካትት ይችላል፣ በመጎንተል፣ ፀጉር በመሳብ፣ በመቧጨር፣ ወዘተ) ሁለቱም ወገኖች አስተዋጽኦ ያደረጉበት የእርስ በርስ ድብድብ። ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በደል ወይም ጉዳት የማድረስ ዓላማው ላይ ነው። | | ■ ደረጃ 2 (Elem) | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |
| በሌላ ግለሰብ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስን የሚያጠቃልል ሁለቱም ወገኖች አስተዋጽኦ ያደረጉበት የእርስ በርስ ድብድብ። | | | ■ ደረጃ 3 (Elem) | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| ማሾፍ/መሳለቅ፣ ማታለል፣ ሽብር መንዛት፣ እና/ወይም ድብድብን ማበረታታት፣ ረብሻ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ህግጋትን መጣስ፣ ወይም ጠብ / ድብድብን መቅረፅ። | ■ ደረጃ 1 (Elem) | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |

## ቁማር (GM)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ለጨዋታው በመወራረጃነት የሚቀርበው ነገር ምንም ይሁን ምን እርግጠኛ ባልሆነ ውጤት ላይ የሚከናወን ውርርድን የሚያካትቱ ትምህርታዊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች፤ እውነተኛ ወይም ምሳሌያዊ ዋጋ ያለው ነገርን ሊበላ ወይም ሊጠፉ የሚያስችል ነገርን ባካተተ በማንኛውም የእድል ጨዋታ ላይ መሳተፍ። ምሳሌዎቹም እርግጠኛ ያልሆነ ውጤት ባላቸው ተግባራት፣ የቤት ስራ፣ ውድድር እና ጨዋታዎች ላይ መወራረድን የሚያካትት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ ኤገደብም። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |

## ትንኮሳ/ማስፈራራት (HI)

አስፈላጊ ንዑስ ኮድ፡- HD – በአካል ጉዳት ላይ ተመሰርቶ የሚቃጣ ትንኮሳ፣ HR – በዘር/በብሔር ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ትንኮሳ፣ HS – በፆታ ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ትንኮሳ፣ HSO – በፆታዊ ዝንባሌ ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ትንኮሳ፣ HBR – በሐይማኖት ላይ ተመስርቶ የሚቃጣ ትንኮሳ፣ HOTH – በሌሎች ላይ የሚቃጣ ሌላ ማንኛውም ትንኮሳ

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በፆታ፣ በፆታዊ ማንነት፣ በፆታ አገላለፅ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በፆታዊ ዝንባሌ፣ በብሔር፣ በዘር ሐረግ፣ በአካል ጉዳት ወይም በህግ ጥበቃ በሚደረግለት ሌላ በማንኛውም ባህሪ ላይ የተመሰረተ ያልተፈለገ አካላዊ ንክኪ ወይም የቃል፣ የጽሁፍ ወይም ምሳሌያዊ ቋንቋ። ህገወጥ የትንኮሳ ምሳሌዎችም የሚያካትቱት፣ በዘር ላይ ተመስርተው የሚሰነዘሩ ቀልዶች ወይም አስተያየቶች፤ በፆታዊ ግንኙነት እንዲመለሱ የሚቀርቡ የውለታ ጥያቄዎች እና ተገቢ ያልሆነ ፆታዊ ግንኙነትን የሚሹ ድርጊቶች፣ የግድግዳ ስእል፣ በተለያዩ ስሞች ጠቅሶ መሳደብ፣ ወይም ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ወይም ጥበቃ በሚደረግላቸው ባህሪያት ላይ በመመስረት የጥላቻ ተግባራትን መፈጸም። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| ዛቻ/ማስፈራሪያ ሆን ተብሎ የሚከናወን ባህሪ ሲሆን የተለመዱ ስሜታዊ/ሥነ ልቦናዊ ምላሾችን በሚሰጥ መደበኛ ሰው ላይ በደል ወይም ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ እንዲፈራ የሚያደርግ ክስተት ነው። ባህሪው ኃይለኛ በመሆኑ ያደርሳል ተብሎ የተነገረውን ፍራቻ እንዲፈጥር ወይም ተጎጂው በትክክል መፍራቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም. ማንኛውም በትንኮሳ/በማስፈራራት አውድ ስር የተሰጠ ትርጉምን የሚያሟላ ነገር ግን በተለይ በህግ ጥበቃ በሚደረግላቸው ክፍሎች ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ላይ ያላነጣጠረ ማንኛውም ድርጊት HOTH-ትንኮሳ ተብሎ በንዑስ ኮድ መቅረብ ይኖርበታል። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| ተደርጓል ተብሎ የተጠረጠረው ትንኮሳን ለመከታተል ጥቅም ላይ ይውላል። ድርጊት ፋፃሚውን መለየት በማይቻልበት ወቅት ተደርጓል ተብለው የተጠረጠሩ የትንኮሳ/የማስፈራራት ክስተቶች ሲኖሩ ለ OCR ሪፖርት ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ኮድ አንድ ሰው በሚያቀርበው በማስረጃ ሊረጋገጡ የማይችሉ ወይም የትንኮሳ ልዩ መመዘኛዎችን የማያሟሉ የትንኮሳ ደርሶብኛል ጥያቄዎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር ጥቅም ላይ መዋል አለበት። | | ■ ደረጃ 2 | | | |

## ተንኮል መስራት (HAZE)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| አንድ ምክንያታዊ የሆነ ሰው በተማሪው አእምሮአዊ ወይም አካላዊ ጤንነት ወይም ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል ብሎ ማመን እንዲችል የሚያደረግ ወይም ተማሪውን ለማነሳሳት፣ ለመቀበል፣ በማንኛውም ቡድን፣ ክፍል፣ አደረጃጀት፣ ክለብ ወይም የአትሌቲክስ ቡድን አባልነት ለማስተናገድ ዓላማዎች አዋራጅ ወይም አስጨናቂ በሆነ ሁኔታዎች ላይ የሚያስቀምጥ ተግባር ነው። ሁሉም ተሳታፊ ተማሪዎች በፈቃደኝነት የሚሳተፉ ቢሆኑም ተንኮል (Hazing) ሊከሰት ይችላል። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ተገቢ ያልሆነ እቃ /ተቀጣጣይ ቁስ (IO)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| እሳት ለማስነሳት ወይም ለማቀጣጠል ጥቅም ላይ የሚውሉ ክብሪት፣ ላይተሮች፣ ኬሚካሎች ወይም ሌሎች መሳሪያዎችን ጨምሮ ለት/ቤት መቼት ተገቢ ያልሆነ ቁስ በአካል ይዞ መገኘት። ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች የግድ ተቀጣጣይ መሆን የለባቸውም (ለምሳሌ፣ የአሻንጉሊት ጠመንጃዎች፣ ከ <4 ኢንች ያነሰ ስለት ያለቸው ትናንሽ ቢላዎች፣ የሼል ማስቀመጫዎች፣ ወይም እንደ ድንጋይ ያለ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሶች)። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |

## አለመታዘዝ (IS)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ለትምህርት ቤት ህግጋት ወይም ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች መመሪያ አለመታዘዝ | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| አዋቂዎች ትዕዛዝ ሲሰጡ ጠብ ወይም ረብሻን መተው አለመቻል | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| መተላለፍ | | ■ ደረጃ 2 | | | |
| ሌላ ሰውን ወደ ውስጥ ለማስገባት ሲባል የደህንነት ማስጠበቂያ የውጭ በሮችን ክፍት ማድረግን ጨምሮ የትምህርት ቤት ደህንነት ፕሮቶኮሎችን መጣስ | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |

## ታማኝነት (INT)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| መዋሸት -- መረጃን ማጥፋት፣ ለማታለል መሞከር፣ ወይም ለአዋቂዎች ወይም ለእድሜ እኩ እውነታውን አለመናገር። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| መስረቅ -- ያልተፈቀደ የ AI አጠቃቀምን ጨምሮ፣ በመምህሩ ከተፈቀደው ውጪ በሆነ መንገድ መረጃን፣ ጥያቄዎችን ወይም መልሶችን ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| ማጭበርበር -- የሌሎችን ሥራ ወይም ሰነዶች በሐሰት ፊርማ ማቅረብ | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |

## ሳያስፈቅዱ መውጣት (LWP)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሳያስፈቅዱ ከመመሪያ ክፍል/ቡድን መውጣት | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| ከክፍል/ቡድን ሳያስፈቅዱ ከ 20 ደቂቃ በላይ ለቆ መውጣት እና የአስተዳደር መመሪያዎችን ለማክበር ፈቃደኛ አለመሆን። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| ሳያስፈቅዱ የትምህርት ቤት ህንፃውን ለቆ መውጣት | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |
| ሳያስፈቅዱ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢውን ለቆ መውጣት | | ■ ደረጃ 2 (Elem) | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ተግባራዊ ሳይደረግባቸው ያመለጡ መዘዞች (MCS)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በትምህርት ቤቱ የተላለፉ የዲሲፕሊን ግድፈት መዘዞችን ማምለጥ | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |

## ሌሎች (OTH)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የሚከሰተው ጥፋት፣ የትምህርት ቤት ህግጋትን ወይም ፖሊሲዎችን በመጣስ የትምህርት ቤቱን ሰላማዊ መንፈስ የሚረብሽ ሲሆን ይህ ምድብ ከላይ ከተዘረዘሩት በአንዱ የመብት ጥሰት መግለጫ ስር ላልወደቁ የዲሲፕሊን ጥሰቶች ሊያገለግል ይችላል። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## አካላዊ ንክኪ (PHY)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በደል ወይም ጉዳት ለማድረስ ዓላማ ያላደረገ መግፋት/መንሸም/መምታት። ድርጊቶች፣ የተደጋጋሚነት ፅባይ ያላቸው፣ የተለየ ምድብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |

## የንብረት ጉዳት/ሆን ተብሎ የሚፈፀም የንብረት ውድመት (PD)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በትምህርት ቤቱ፣ በሠራተኞች ወይም በተማሪዎች የግል ንብረት (ቴክኖሎጂን ጨምሮ) ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ ወይም ለመጉዳት መሞከር | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| በህግ የተደነገጉ መስፈርቶችን በመጣስ የሚፈፀም ከባድ ንብረትን የማውደም ወንጀል ጥፋት። ከህግ አስከባሪዎች ጋር መማከርን ይጠይቃል። | | | | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ወሲብ ነክ መጥፎ አመል/ፆታዊ ትንኮሳ (SM)

ምስሎች/ቪዲዮዎች ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን የሚያካትቱ ከሆኑ ለሕግ አስከባሪ አካላት እና ለሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች ማስታወቅ ያስፈልጋል።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በቃል፣ በፅሁፍ፣ በምልክት ቋንቋ፣ ማጋለጥ (ወሲብ ነክ ለሆነ ይዘት) ወይም አላስፈላጊ የሆነ እና ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው አካላዊ ንክኪ. ለምሳሌ, መቆንጠጥ፣ ጡቶችን፣ መቀመጫን፣ ግላዊ የሆኑ ቦታዎችን መያዝ ወዘተ. ይህ ኤሌክትሮኒካዊ የሆነ "ወሲብ ነክ መልዕክት መፃፍን" ያካትታል። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በሚደረጉ ኩነቶች ወቅት ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ምስሎችን ወይም ቅጂዎችን ይዞ መገኘት። | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በሚደረጉ ኩነቶች ወቅት ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ምስሎችን ወይም ቅጂዎችን ማሰራጨቱት። | | | | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| ማፍቀርን መግለፅ ጨምሮ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ድርጊቶች። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ማርፈድ (TAR)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| እስከ 5 ደቂቃ አርፍዶ መድረስ ከ 5 ደቂቃ በላይ አርፍዶ መድረስ | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |

## ስርቆት (TH)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| የሆነ ነገር መውሰድ፣ የሆነ ነገር ለመውሰድ መሞከር ወይም የእራስ ያልሆነ ነገርን ይዞ መገኘት። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| በህግ የተደነገጉ መስፈርቶችን በመጣስ የሚፈፀም ከባድ የስርቆት ወንጀል። ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር መማከርን ይጠይቃል። RSMo Section 570.030 | | | | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ዛቻ/የቃላት እሰጣገባ (T)

የዛቻውን ትክክለኛነት እና ክብደት ለማወቅ በተቃጣው ዛቻ ላይ ግምገማ ይካሄዳል–ጊዜያዊ ወይም ጉልህ/ተጨባጭ ስለመሆኑ።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በአካል ላይ ጉዳት ይደርሳል የሚል ስጋት የማይፈጥሩ በሌላ ሰው ላይ የሚቃጣ የቃላት፣ የጽሁፍ እና ቃል አልባ ዛቻዎች። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | | | |
| ጊዜያዊ ዛቻዎች፣ በዛቻ ግምገማ በሚወሰነው መሰረት፣ በኤሌክትሮኒክ፣ በቃላት፣ በጽሁፍ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ በግል ወይም በትንንሽ ቡድኖች ላይ የሚቃጣ ጥቃት። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| ጸያፍ ቃላት መጠቀምን ሊያካትት ወይማ ላያካትት የሚችል ነገር ግን የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ መስተጓጎል የሚያስከትል ከሌሎች ተማሪዎች ወይም አዋቂዎች ጋር የሚፈጸም የቃላት እሰጣገባ፣ ። | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |
| በፍጥነት ተለዋዋጭ ድርጊቶች – ት/ቤትን፣ በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የሚደረጉ ተግባራትን ወይም ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጪ የሚካሔዱ እና በትምህርት ቤቱ ክትትል የሚደረግባቸው እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚረብሽ ብጥብጥ፣ ወይም አስጊ ባህሪ። በአስጊ ሁኔታ ግምገማ የሚወሰኑ ተጨባጭ ስጋቶች። ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር መማከርን ይጠይቃል። | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| በአስጊ ሁኔታ ግምገማ የሚለዩ በሌላ ሰው (ዎች) ላይ ሚሰነዘሩ፣ ጉልህ ስጋት የሚፈጥሩ ዛቻዎች። የሽብር ዛቻዎችንም ሊያካትት ይችላል። ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር መማከርን ይጠይቃል። | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |
| ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም (ማለትም በ Snapchat፣ Twitter፣ Facebook፣ ወዘተ. ጨምሮ ነገርግን በዚህ ብቻ የማይገደብ) በሌላ ሰው (ዎች) ላይ የሚሰነዘሩ፣ ወይም መስተጓጎልን ለመፍጠር ያለሙ ጉልህ ዛቻዎች። | | | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | ■ ደረጃ 5 |

## ትምባሆ/ኒኮቲን ወደ ውስጥ መሳቢያ ዘዴ (TB)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ማንኛውንም የትምባሆ ምርት ወይም የኒኮቲን መሳቢያ (ማለትም ኤሌክትሮኒክ ሲጋራ) ይዞ መገኘት እና/ወይም መጠቀም። | | ■ ደረጃ 2 | | | |
| የ "ቬፕ" ብዕር ይዞ መገኘት እና/ወይም መጠቀም | | ■ ደረጃ 2 | | | |
| የኒኮቲን መሳቢያ ቁሶችን ማሰራጨት | | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | ■ ደረጃ 4 | |

## መቅረት (TR)

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ማንኛውም ተማሪ እድሜው ምንም ይሁን ምን ያለ በቂ ምክንያት ከክፍል ወይም ከትምህርት ቤት መቅረት፣ በዕለቱ ከ 10 ደቂቃ በላይ የሆነ ከክፍል መቅረት ቢሆንም አንኳን፣ እንደ ቀሪ ይቆጠራል። መቅረት ሲባል በአብዛኛው ያለወላጆች እውቅና የሚከሰት መቅረትን የመሚያጠቃልል ሲሆን፣ በወላጆች እውቅናም ቢሆን እንደ ቀሪ የሚቆጠርባቸውም አጋጣሚዎች አሉ። | ■ ደረጃ 1 | ■ ደረጃ 2 | ■ ደረጃ 3 | | |

## የጦር መሳሪያ (W)

ይህ ኮድ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜም የህግ አስከባሪ አካላትን ማሳወቅ ያስፈልጋል።

| ባህሪ | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 | ደረጃ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| በ FHSD ቦርድ ፖሊሲ ላይ እንደተገለጸው ማንኛውንም የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት። | | | | | ■ ደረጃ 5 |
| በ FHSD ቦርድ ፖሊሲ ላይ እንደተገለጸው ማንኛውንም የጦር መሳሪያ መጠቀም። | | | | | ■ ደረጃ 5 |
| በ FHSD ቦርድ ፖሊሲ ላይ እንደተገለጸው ማንኛውንም የጦር መሳሪያ መሸጥ፣ መጠየቅ እና/ወይም ማሰራጨት። | | | | | ■ ደረጃ 5 |

# የዲሲፕሊን ትርጓሜዎች

**የዲቴንሽን ጥናት ክፍል/አዳራሽ**

ከትምህርት ሰዓታት ውጭ ጥቅም ላይ የሚውል ቁጥጥር የሚደረግበት የጥናት ክፍል/አዳራሽ ነው። የቅዳሜ ትምህርት ቅዳሜ ጧት የሚሰጥ ቁጥጥር የሚደረግበት የጥናት ክፍል/አዳራሽ ነው። ሰዓቱ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ይለያያል። የተማሪው ተግባራት በቅርበት ክትትል የሚደረግበት እና ገደብ የተጣለበት ነው። ተማሪዎች የዲቴንሽን ጊዜ ቆይታቸው በሙሉ ፀጥ እንዲሉ እና በተሰጣቸው ተግባራት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ይጠበቃል። ወደ ዲቴንሽን ክፍል ዘግይተው የሚደርሱ ተማሪዎች የተመደበላቸውን የዲቴንሽን ቅጣት ቆይታ እንዲያጠናቅቁ አይፈቀድላቸውም።

**በት/ቤት ውስጥ ከመደበኛ ክፍል ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል (ISS/ ISAP)**

ተማሪው ውጤት የሚያስገኙ የቤት ስራዎችን እንዲጨርስ እድል የሚሰጥ የተዋቀረ፣ ራሱን የቻለ ከባቢ ነው። ተማሪው ISS/ISAP ውስጥ ከመመደቡ በፊት ወላጅ/አሳዳጊዎች እንዲያውቁት ይደረጋል። IEP ያለው ተማሪ ISS/ISAP ውስጥ ከተመደበ፣ የሚሰው የልዩ ፍላጎት ትምህር አገልግሎት በ IEP ውስጥ በተገለፀው መሰረት የሚቀርብለት ይሆናል አሊያም በ ISS/ISAP ውስጥ የሚኖረው ቆይታ ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ እንደተጣለበት ተደርጎ ይቆጠራል። አንድ ተማሪ በት/ቤት ውስጥ ከመደበኛ ክፍል ውጪ ሆኖ እንዲቆይ የተጣለበት እገዳን ሲያጠናቅቅ ከትምህርት ሰዓት በኋላ እንዲሰሩ የሚሰጡ ተግባራት ላይ ሊሳተፍ ይችላል።

**ከት/ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ መጣል (OSS)**

ትምህርት ቤት ተገኝቶ ትምህርት እንዳይከታተል ማባረር ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ አስቀድሞ ተማሪን እና በወላጅ/አሳዳጊን ያካተተ ጉባኤ ሊያስፈልግ ይችላል። ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር ከትምህርት ቤት ውጭ ሆነው እንዲቆዩ እገዳ የተጣለባቸው (OSS) ተማሪዎች ያመለጣቸውን 100% ትምህርት የማካካስ እድል ይኖራቸዋል፡፡

በእገዳ ወቅት የሚኖረው ተማሪው ውጤት ተማሪው በታገደበት ወቅት ከመደበኛ ትምህርት ክፍል ውጭ ሆኖ እንዲያጠናቅቅ ተሰጥቶት በነበረው ስራ ላይ መሰረት ያደርጋል። ለተማሪው አማራጭ የትምህርት ቦታ ተሰጥቶት ተማሪው ይህን ቦታ ካልተቀበለ/ውድቅ ካደረገ፣ ወላጅ(ወላጆች)/አሳዳጊ (አሳዳጊዎች) ተማሪው በተጣለበት እገዳ ወቅት ማግኘት የሚገባውን ትምህርትን በተመለከተ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ተማሪው ምንም የማካካሻ ስራ እንዲያገኝ ይፈቀድም:-

- በተገቢው ቀን ያልቀረበ የ OSS ተመላሽ ሥራ
- ተማሪው ወደ ክፍል በተመለሰበት ቀን ያልተጠናቀቀ የ ISS/ISAP ሥራ
- ተማሪ/ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) AIP (አማራጭ የጣልቃ ገብነት መርሃ-ግብር) ላለመውሰድ ከመረጡ
- እገዳው ከ 55 የትምህርት ቀናት በላይ ከቆየ

ከትምህርት ቤት የታገደ ማንኛውም ተማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ በተጣለበት ወቅት በትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በሌላ የዲስትሪክቱ ንብረት ውስጥ መገኘት የለበትም። በተጨማሪም፣ የታገደ ተማሪ በእገዳው ቆይታ ወቅት በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥም ሆነ ከግቢው ውጭ በማናቸውም ከስርዓተ-ትምህርቱ ውጭ በሆኑ ተግባራት ላይ መሳተፍም ሆነ መከታተል አይችልም። ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ የተጣለበትን እገዳ ከጨረሰ በኋላ፣ ተማሪው በክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ከመሳተፉ ወይም ከመወዳደሩ በፊት እንደገና በት/ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ አመኔታን እና ክብርን መልሶ ለማግኘት እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። ነገርግን፣ ተማሪው የስነ ምግባር ኮሚቴ በሚያከናውነው ችሎት ላይ እንዲሳተፍ እንዲሁም በምድብ ተለዋጭ መርሃ-ግብር ላይ ለመሳተፍ በዲስትሪክቱ ንብረት እንዲገኝ ይፈቀድለታል።

ከትምህርት ቤት-ውጭ ሆኖ እንዲቆይ ተጥሎ የነበረ እገዳን ተከትሎ ወደ ትምህርት ቤት የሚመለስ ማንኛውም ተማሪ ርዕሰ-መምህሩን/ተወካዩን በሚያሳትፍ እና የተማሪውን ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ባካተተ መልኩ የመልሶ-መግቢያ ስብሰባ ላይ መገኘት አለበት።

**ከ 10 እስከ 180 ቀናት ከትምህርት ቤት ውጪ ሆኖ እንዲቆይ የተጣለ እገዳ**

የት/ቤቱ ተቆጣጣሪ/ተወካዩ አንድ ተማሪን እስከ 180 የትምህርት ቀናት ድረስ ከትምህርት ቤት ውጪ ሆኖ እንዲቆይ ሊያግድ እና ለትምህርት ምክር ቤቱ ረዘም ያሉ እገዳዎች እንዲጣሉበት ብሎም እንዲባረር ምክረ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል። ከመቶ ሰማንያ (180) ቀናት በላይ የሆኑ እገዳዎችን ሊጥል

የሚችለው ምክር ቤቱ ብቻ ነው። የመጀመሪያው እገዳ እንዲጣልበት ያስቻለውን ባህሪ ለመገምገም እና ከአሥር (10) ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ማገድን እና/ወይም ማባረርን በተመለከተ ምክረ ሀሳብ ለመስጠት የስነ ምግባር ኮሚቴው ችሎት ሊሰየም ይችላል።

**የስነ ምግባር ችሎት ኮሚቴ**

የስነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴው ከአሥር (10) የትምህርት ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ውጪ ሆኖ እንዲቆይ የሚጣል የትኛውም እገዳ ከመተግበሩ በፊት የስነ ምግባር ችሎት ላይ ይሰየማል። የስነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የችሎቱን ሹም፣ ርዕሰ-መምህሩን/ተወካዩን እና ሌሎች የሕንፃ ወይም የዲስትሪክቱ ሠራተኞችን ሊያካትት ይገባል። ተማሪው እና ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በስነ-ምግባር ኮሚቴው ችሎት ላይ የመገኘት እድል ይሰጣቸዋል። ችሎቱ ተማሪው ላይ በተጣለው የመጀመሪያ አስር (10) የትምህርት ቀናት እገዳ ወቅት ይካሄዳል። ጠበቃዎች በሥነ-ምግባር ኮሚቴው ችሎት ላይ መገኘት አይፈቀድላቸውም (ወላጅ/አሳዳጊ እራሳቸው ጠበቃ ሆነው ከልጃቸው ጋር ካልተገኙ በስተቀር) ። ወላጅ/አሳዳጊ ያለባቸው የአካል ጉዳትን ለማስተናገድ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በሥነ-ምግባር ኮሚቴው ችሎት ወቅት የድምፅ/ምስል መቀረጫ መሳሪያዎችን መጠቀም አይፈቀድም። የድምፅ/ምስል መቀረጫ መሳሪያዎችን የመጠቀም አስፈላጊነት ማሳወቂያ ችሎቱ ከመሰየሙ ቢያንስ ከ 48 ሰዓታት በፊት ለተማሪ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት መቅረብ አለበት።

በትምህርት ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ተወካይ አማካኝነት ከአስር (10) ቀናት በላይ እገዳ ሲጣል፣ ተማሪው የዚህ እገዳ ማስታወቂያ በደረሰው በአሥር (10) ቀናት ውስጥ፣ በችሎቱ ያልታየ መረጃ እንዳላቸው ካመኑ ለሥነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴው ለትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄ የይግባኝ ጥያቄው በሚቀርብበት ቀን ከጠዋቱ 4:30 በፊት በዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ ውስጥ መድረስ አለበት። ጠበቆች የይግባኝ ችሎቱ ላይ ከትምህርት ቤቶቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ጋር እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም።

የተማሪው ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) የትምህርት ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ውሳኔን ከተቃወሙ በትምህርት ምክር ቤት ችሎት ፊት ቀርበው ጥያቄ ሊቀርብ(ቡ) ይችላል(ሉ)። እንዲህ ዓይነት ችሎት የሚጠይቅ ተማሪ በተማሪው ላይ የቀረቡ ክሶች፤ ችሎቱ የሚካሄድበት ሰዓት፣ ቀን እና ቦታ፤ እንዲሁም ተማሪው በአማካሪ የመወከል፣ ምስክሮችን የመጥራት እና መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ፣ እንዲሁም ተማሪው መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት እንዳለው በጽሑፍ ይገለፅለታል።

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት (የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች) ዲሲፕሊን መመሪያ**

አሁን ላይ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች በግዛትና በፌዴራል ህጎች/መመሪያዎች መሠረት የዲሲፕሊን ጉዳያቸው የሚታይ ይሆናል። የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ለሥነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴ ጉዳያቸው እንዲታይ ምክረ ሀሳብ ቀርቦ የዚያ ችሎት ውጤት ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ መታገድን የሚያስከትል ከሆነ፣ የችሎት ሂደቱን ተከትሎ ጥሰቱ ከተማሪው የአካል ጉዳት ጋር የተዛመደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን የማብራሪያ ውሳኔ ስብሰባ ይካሄዳል።

**በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ የ A+ ዜግነት ፖሊሲ**

የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የ A+ አማካሪ ኮሚቴ በ A+ ደረጃ ለሚመረቅ ተማሪ መልካም ዜግነት በጣም አስፈላጊ ነው ብሎ ያምናል። በ A+ መርሃ–ግብር ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች እገዳ ሲጣልባቸው ብቁነታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል። ሁሉም አራት የትምህርት ዓመታት ቆይታ የዜግነት መዝገቡ አካል ናቸው። የሚከተሉት ጉዳዮች ከ A+ መርሃ–ግብር መወገድን ያስከትላሉ:-

- በተማሪው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታ (ከ 9- 12ኛ ክፍሎች) ውስጥ 5 ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ በትምህርት ቤት ውስጥ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ ሆኖ እንዲቆይ እገዳ ካጋጠመው።
- ከ 10 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ከትምህርት ቤት ውጭ ሆኖ እንዲቆይ የሚያስገድድ ማንኛውም እገዳ።

**የ A+ ይግባኝ ሂደት**

አንድ ተማሪ እና/ወይም ወላጅ/አሳዳጊ በክፍል የመገኘት ፖሊሲ ወይም የዜግነት ህግ ጥሰት ማሳወቂያ ከተቀበለ በኋላ የ A+ ይግባኝ መጠየቅ መብት አላቸው። በአሳሳቢ ጉዳዮች ወይም ብቁ አለመሆን ሲከሰት፣

- ተማሪው እና ወላጅ/አሳዳጊ አሳሳቢ የሆነባቸውን ጉዳይ ወይም ብቁ አለመሆንን በተመለከተ ለመወያየት ያላቸውን ፍላጎት ለ A+ አስተባባሪው በጽሑፍ ማሳወቅ አለባቸው።
- የ A+ አስተባባሪው ብቁነትን ከግምት ውስጥ ለማስገባት የ A+ ይግባኝ ኮሚቴ ስብሰባን ይጠራል።
- የ A+ ይግባኝ ኮሚቴው ጥያቄውን ይሰማና ውሳኔውን ለተማሪው እና ለወላጅ/አሳዳጊ ያሳውቃል። ይግባኝ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ A+ አስተባባሪ የሚያገኘውን የ "A+ ይግባኝ" ቅጽ መሙላት አለበት። የግምገማ ኮሚቴው ውሳኔ ላይ ከደረሰ በኋላ፣ የ A+ አስተባባሪው ለወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ያሳውቃል።

**መባረር**

መባረር የሚለው ቃል ከትምህርት ቤት በቋሚነት መወገድን ያመለክታል። የረጅም ጊዜ እገዳ ከመጣል በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ለትምህርት ምክር ቤቱ ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲባረርም ምክረ ሀሳብ ሊያቀርብ ይችላል። ምክር ቤቱ እንደዚህ ያሉ የውሳኔ ምክረ ሃሳቦችን በመገምገም የማባረሪያ ችሎት ለመቀመጥ ወይም ላለመቀመጥ ይወስናል። የትምህርት ምክር ቤቱ የማባረሪያ ችሎት ለመቀመጥ ከወሰነ ተማሪው እና ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በተማሪው ላይ የቀረቡ ክሶችን፤ የችሎቱን ጊዜ፣ ቀን እና ቦታ፤ እንዲሁም ተማሪው በአማካሪ የመወከል፣ ምስክሮችን የመጥራት እና መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ፣ እንዲሁም ለተማሪው መከላከያ ሌላ ማስረጃ የማቅረብ መብት እንዳለው በጽሑፍ ይገለፅላቸዋል። ማንም ተማሪ በትምህርት ምክር ቤት ፊት ችሎት ቀርቦ ጉዳዩ ሳይሰማ ሊባረር አይችልም።

በዲስትሪክቱ መመሪያ 2660 መሰረት፣ ማንኛውም ተማሪ ከዲስትሪክቱ ወይም ከሌላ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት እገዳ ተጥሎበት ወይም እንዲባረር መደረጉን ተከትሎ ዲስትሪክቱ ተማሪው ተመልሶ መመዝገብ መቻል አለመቻሉን ለመወሰን ስብሰባ እስከሚያካሂድ ድረስ ተማሪው (በህግ ካልተፈቀደለት በስተቀር) ተመልሶ ሊመዘገብ ወይም ትምህርት ቤት ተመልሶ እንዲገባ ሊፈቀድለት አይችልም። በስብሰባው ወቅት፣ ተሳታፊዎች ቅጣት ያስከተለውን ባህሪ እና ወደፊት ተመሳሳይ ተግባራት እንዳይከሰቱ ለመከላከል አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመኑ ማናቸውንም የማስተካከያ እርምጃዎች ከግምት ውስጥ ያስገባሉ።

ነገርግን፣ ማንኛውም ተማሪ በአዋቂ ፍርድ ቤት ተከስሶ ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ ወይም በአፍላ ወጣቶች ፍርድ ቤት በወንጀል ተከስሶ፣ ነገር ግን ጉዳዩ እስካሁን እልባት ሳያገኝ ወይም ውሳኔ ሳይሰጥበት ከቀረ፣ ወይም በአፍላ ወጣቶች ፍርድ ቤት በወንጀል ከተፈረደበት ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ እንዲገባ ወይም እንዲመዘገብ አይፈቀድለትም፣ እንደአዋቂ ከተከሰሰ፣ ከሚከተሉት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን ፈፅሟል ማለት ነው፦

- አንደኛ ዲግሪ የግድያ ወንጀል (Mo. Rev. Stat. § 536.020)
- ሁለተኛ ዲግሪ የግድያ ወንጀል (Mo. Rev. Stat. § 565.021)
- አንደኛ ዲግሪ የጥቃት ወንጀል (Mo. Rev. Stat. § 565.050)
- አስገድዶ መድፈር (Mo. Rev. Stat. § 566.030)
- አስገድዶ ግብረ ሰዶም መፈፀም (Mo. Rev. Stat. § 566.060)
- የአንደኛ ዲግሪ ዝርፊያ (Mo. Rev. Stat. § 570.023)
- ለአካለ-መጠን ላልደረሱ ልጆች የአደንዛዥ ዕጾችን ማሰራጨት (Mo. Rev. Stat. § 579.020)
- አንደኛ ዲግሪ የእሳት አደጋ ማስነሳት ወንጀል (Mo. Rev. Stat. § 569.040)
- ጠለፋ እንደ ክፍል A ወንጀል (Mo. Rev. Stat. § 565.110)
- ለአካለ መጠን ካልደረሰ/ች ልጅ ጋር የሚደረግ ጾታዊ ግንኙነት (Mo. Rev. Stat. § 566.032)
- ለአካለ መጠን ካልደረሰ/ች ልጅ ጋር የሚደረግ የግብረ ሰዶም ተግባር (Mo. Rev. Stat. § 566.062

## የተማሪዎች የአልኮል እና የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ አጠቃቀም

የትምህርት ምክር ቤቱ ትምህርታቸውን በፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት የሚከታተሉ ተማሪዎች ጤና፣ ደህንነት እና ጥበቃን በተመለከተ ያለው የኃላፊነት ድርሻ ምን እንደሆነ ይገነዘባል። ስለዚህ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ/ንብረት ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ወይም ኩነቶች፣ በመስክ ጉዞዎች ወይም ለትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ ተማሪዎችን በማጓጓዝ እያገለገለ ባለ በየትኛውም ተሽከርካሪ ውስጥ አልኮል ወይም አደንዛዥ ዕፆችን መጠቀም፣ መሸጥ፣ ማስተላለፍ፣ ይዞ መገኘት ወይም ተጠቅሞ በተፅእኖ ስር መሆን የተከለከለ ነው።

አልኮል፣ በዚህ የተማሪ ሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው፣ እንደ አልኮል፣ "አልኮል ነክ ያልሆኑ" የብቅል መጠጦች አሊያም አልኮል ወይም "የአልኮል ነክ ያልሆኑ" የብቅል መጠጦችን የሚወክሉ ንጥረ-ነገሮች ተብሎ ይተረጎማል።

አደንዛዥ ዕፆች፣ በዚህ የተማሪ ሥነ-ምግባር ደምብ ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው፣ እንደ አስካሪ፣ ሕገ-ወጥ አደንዛዥ ዕፆች፣ በሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ ህጋዊ ሰው ሰራሽ ንጥረ ነገሮች፣ አካላዊ/አእምሯዊ እክል/መሳን የሚያስከትሉ ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድኃኒቶች እና/ወይም አካልን ወይም አእምሮን የሚለውጡ ኬሚካሎች ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ-ነገሮች፤ ወይም አስካሪ ንጥረ ነገሮች፣ ሕገ-ወጥ ዕፆች፣ በሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድኃኒቶች፣ ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ ህጋዊ ሰው-ሠራሽ ንጥረነገሮች ወይም አካላዊ/አእምሯዊ እክል/መሳን የሚያስከትሉ ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድኃኒቶች፣ እና/ወይም አካልን ወይም አእምሮን የሚለውጡ ኬሚካሎች ወይም ከተሰሩበት አገልግሎት ውጭ ለሆነ ዓላማ የሚውሉ ያለ ሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድኃኒቶች፤ ወይም የመድኃኒት መውሰጃ ቁሶች ተብሎ ይተረጎማል።

በትምህርት ቤት ዲስትሪክቱ ውስጥ ማንኛውንም ብቁ የሆነን ሰው ትምህርት እንዳያገኝ መከልከል የምክር ቤቱ ወይም የትምህርት ቤቱ አመራር እንዲሁም አስተዳደር ዓላማ ባይሆንም፣ ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደትን ለመፍጠር መልካም የትምህርት ቤት ዲሲፕሊን እና የትምህርት ቤት ዜግነት አስፈላጊ እንደሆነ ይታወቃል። በአደንዛዥ ዕፆች ወይም በአልኮል ተፅዕኖ ስር በወደቁ ወይም እነዚህን ዕፆች በያዙ ተማሪዎች ምክንያት

ለሚከሰቱ አላስፈላጊ መታወኮች እና መዘናጋቶች ትምህርታቸውን እና የሚሰጧቸውን ተግባራት እንዲሁም የተፈጠረላቸውን መልካም የመማር አጋጣሚ በደንብ መጠቀም የሚፈልጉ ተማሪዎችን ማጋለጥ ፍትሃዊ አይደለም።

በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ ተፅእኖ ስር ወድቆ ወይም ይዞ የተገኘ ተማሪ እስከ 180 የትምህርት ቀናት ጊዜ ድረስ ከትምህርት እገዳ ሊጣልበት ወይም ሊባረር ይችላል። ርዕሰ-መምህሩ/ተወካዩ እንደዚህ ያሉ ተማሪዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ሊያግዷቸው ይገባል። ለመጀመሪያው የአልኮል ወይም የአደንዛዥ ዕፅ ይዞ መገኘት ወይም በተፅዕኖ ስር የመውደቅ ደንብ ጥሰቶች፣ በ 10-ቀናት የትምህርት እገዳ ምትክ ተማሪው በፍራንሲስ ሀውል ኒየን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚሰጠው አማራጭ የጣልቃ ገብነት መርሃ-ግብር (AIP) ላይ ለመሳተፍ መምረጥ ይችላል።

በ AIP መርሃ ግብሩ፣ ተማሪው ምን ዓይነት የአደንዛዥ እፅ/የአልኮል አጠቃቀም ባህሪ እንዳለው እና የትኛው አለአግባብ መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል የምክር አገልግሎት እንደሚያስፈልገው ለመወሰን በ FHU ሰራተኞች የመጀመሪያ ቅበላ መነሻ ምዘና ላይ እንዲሳተፍ ይጠበቅበታል። ተማሪው በሙሉ የትምህርት ቀን የሚሰጠውን ትምህርትን በአግባቡ ይከታተላል፣ በትምህርት ሂደቱ የሚሰጡ ሁሉንም የቤት ስራዎች ሰርቶ ያጠናቅቃል እንዲሁም በአደገኛ ዕፅ/አልኮል መጠቀም እና አላግባብ አጠቃቀምን መከላከል ላይ የተዘጋጁ ኮርሶችን ይወስዳል እና/ወይም በምክር አገልግሎት ላይ ተሳትፎ ደርጋል። ይህም በ PreventEd የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወይም አጠቃላይ የአደንዛዣ ዕፅ ግምገማን እንዲሁም በተመረጠ የቤተሰብ ጤና አገልግሎት መስጫ ተማሪው ዕፅ እየተጠቀመ መሆን አለመሆኑ ላይ የማጣሪያ ምርመራ ከተከታይ ምክር አገልግሎት ጋር ሊያካትት ይችላል። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤታቸው ሲመለሱ በአዎንታዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና በአይበገሬነት ግንባታ ላይ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማግኘት ይቀጥላሉ። አንድ ተማሪ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ አስፈጊ የወረቀት ስራዎችን፣ ግምገማውን ወይም ቀጣይ የድጋፍ ስብሰባውን በበቂ ሁኔታ ካላጠናቀቀ፣ የመጀመሪያው የ 10 ቀን እገዳ ይጣላል፣ እና ተገቢ ቅጣት(ቶች) እና/ወይም ተጨማሪ የእገዳ ቀናት ለመወሰን የስነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴ ይካሄዳል። የቅጣቱ(ቶቹ) ምክረ-ሃሳብ ለውሳኔ እንዲያገለግላቸው ለተቆጣጣሪው/ተወካዩ የሚሰጥ ይሆናል።

በተማሪ የስነ-ምግባር ደንብ መሰረት ተማሪው ለሁለተኛ ጊዜ የደንብ ጥሰት ሲፈፅም፣ ጉዳዩ በስነምግባር ችሎት ኮሚቴ ፊት ቀርቦ እስከ 180 የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እንዲታገድ ወይም እንዲባረር ሊደረግ ይችላል።

በህግ ጥሰቱ ክብደት ላይ ተመስርቶ፣ በአልኮል ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሽያጭ፣ ማጋራት ወይም ስርጭት ላይ ተሰማርቶ የተገኘ ተማሪ እስከ 180 ቀናት ከትምህርት ቤት ሊታገድ ወይም ሊባረር ይችላል። እንደዚህ ያሉ ተማሪዎችን ርዕሰ-መምህሩ/ተወካዩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት ሊያግድ ይችላል። ተገቢውን ቅጣት(ቶች) ለመወሰን በመጀመሪያዎቹ አስር (10) የትምህርት ቀናት እገዳ ወቅት የስነ-ምግባር ኮሚቴው ችሎት ሊቀመጥ ይችላል። የቅጣት(ቶች) ምክረ-ሃሳብ ለውሳኔያቸው ያገለግላቸው ዘንድ ለተቆጣጣሪው/ተወካዩ የሚቀርብ ይሆናል። የስነ-ምግባር ችሎት ኮሚቴው ሹም፣ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተለዋጭ የትምህርት ምደባን--ተለዋጭ የመማሪያ ማዕከልን (ALC) የተመለከተ ምክረ ሀሳብ ሊሰጥ ይችላል። እንደዚህ ያለው ምደባ ተቀባይነት ካገኘ፤ ተማሪው ALC በጀመረ ሁለት (2) ሳምንታት ውስጥ፣ በመረጠው የቤተሰብ ጤና አገልግሎት ሰጪ ማዕከል የአደንዛዥ እፅ ግምገማ አድርጎ ማጠናቀቅ አለበት። ተማሪው በመረጠው የቤተሰብ ጤና አገልግሎት ሰጪ ማዕከል የአደንዛዥ ዕፅ የምክር አገልግሎት ክፍለ-ጊዜዎች ላይ እንዲሳተፍ ይጠበቃል።

## ከጠመንጃ-ነፃ ትምህርት ቤቶች

የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ከሁከት-ነፃ የሆነ የትምህርት አካባቢን ለተማሪዎቹ እና የስራ ቦታን ለሠራተኞቹ ማቅረብ ይፈልጋል። ዲስትሪክቱ የጦር መሳሪያ/ጠመንጃ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቦታ እንደሌው ያረጋግጣል።

ዲስትሪክቱ ጠመንጃ/የጦር መሳሪያዎችን ወደ ትምህርት ቤት ይዘው የሚያመጡ ተማሪዎችን አያያዝ በተመለከተ የፌዴራል እና የግዛት ህግጋትን ማክበር እንዳለበት ይገነዘባል። በዚህም መሠረት፣ ይህ መረጃ የ1994 ቱን የአሜሪካ ትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ህግን፣ የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ህግን እና ሌሎች ሊተገበሩ የሚችሉ የፌዴራል እና የግዛት ሕግ ድንጋጌዎችን ያከብራል።

ጠመንጃ/የጦር መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት የሚያመጣ ሰው ለራሱ እና በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባሉ ሌሎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ዲስትሪክቱ ይገነዘባል። የጦር መሳሪያ/ጠመንጃ ይዞ መገኘት ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞችና ለሌሎች ሰዎች ጤና፣ ደህንነት እና ጥበቃ ስጋት የመሆን አቅም እንዳለው ዲስትሪክቱ ይገነዘባል። አንድ ሰው ወደ ትምህርት ቤታችን ቅጥር ግቢዎች ጠመንጃ/የጦር መሳሪያ ሲያመጣ ሊከሰት የሚችለውን የአደጋ ስጋት ዲስትሪክቱ አይታገስም።

ስለሆነም፣ ዲስትሪክቱ እንደሚከተለው ይገልፃል:-

I. ትርጓሜዎች

“ጠመንጃ/የጦር መሳሪያ” የሚለው ስያሜ በቅርቡ በወጣው 18 የዩናይትድ ስቴትስ ህግ ክፍል 921 ላይ በተገለፀው የፌዴራል ሕግ መሠረት ትርጉም ተሰጥቶታል። “ጠመንጃ/የጦር መሳሪያ” የሚለው ስያሜ እንደሚከተለው ያሉ ቁሶችን ያጠቃልላል ነገር ግን በነዚህ ብቻ አይገደብም፦-

a. ቀለህ ያለው ወይም የሌለው የጦር መሣሪያ፣ ክፈፍ ወይም አፈሙዝ እና በመቀጣጠል እና በመፈንዳት አረር ለማስወንጨፍ የተነደፈ ወይም በቀላሉ ወደዚያ ሊቀየር የሚችል ማንኛውም ቁስ፤ ወይም
b. በመፈንዳት ወይም በሌላ ማክነፊያ ድርጊት አማካኝነት አረር የሚያስወነጭፍ ወይም በቀላሉ ወደዚያ ሊቀየር የሚችል እና ቢያንስ ባለግማሽ ኢንች አፈሙዝ ያለው ማንኛውም ቁስ፤ ወይም
c. ማንኛውም ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወይም መርዛማ ጋዝ፣ ለምሳሌ፡- እንደ ቦምቦች፤ የእጅ ቦምብ፤ ከአራት (4) አውንስ በላይ የማክነፊያ ሙሌት ያላቸው ሮኬቶች፤ እና በፌዴራል ሕግ መሠረት እውቅና የተሰጣቸው ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች፤ ወይም
d. በትርጉም ክፍል አንቀጽ B ወይም C ላይ እንደተገለጸው ማንኛውንም መሳሪያ ወደ መሳሪያ ለመቀየር የተነደፉ ወይም የታሰቡ ማናቸውም የክፍሎች ጥምረት።

II. የጦር መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የሚያመጣ ተማሪ፦-

የጦር መሳሪያ/ጠመንጃን ወደ ትምህርት ቤት የሚያመጣ ተማሪን ዲስተሪክቱ አይታገስም። ስለዚህ፣ ዲስትሪክቱ አንድ ተማሪ የጦር መሳሪያ/ጠመንጃ ወደ ትምህርት ቤት ያመጣ መሆኑን ሲደርስበት የሚከተለውን እርምጃ ይወስዳል፦-

a. ዲስትሪክቱ ተማሪውን ተገቢ ወደሆነ የወንጀል ፍትህ ወይም የአፍላ ወጣት ጥፋተኛ ሥርዓት ሊያስተላልፈው ይችላል፤ እንዲሁም
b. ዲስትሪክቱ የደንብ ጥሰቱ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ከአንድ (1) ዓመት (365 ቀናት) ለማያንስ ጊዜ ተማሪውን ከትምህርት ቤት ያግዳል፣ እንዲሁም በተሰጠው ስልጣን ተማሪውን በቋሚነት ከትምህርት ቤት ሊያባርር ይችላል። የበላይ ተቆጣጣሪው ሁኔታዎቹ እንደዚህ ዓይነት ማሻሻያዎችን ለማድግ በምክንያትነት መቅረብ የሚችሉ ከሆነ፣ ይህ የእገዳ ውሳኔ በትምህርት ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ምክረ-ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ሊስተካከል ይችላል።
c. ዲስትሪክቱ፣ በተሰው ስልጣን፣ በዲስትሪክቱ መመሪያ 2620 መሠረት ለታገደ ተማሪ በተለዋጭ ቦታ የትምህርት አገልግሎቶችን ሊያቀርብ ይችላል።

III. የአካል-ጉዳት ባለባቸው ተማሪዎች ላይ ያለው ተፈፃሚነት፡-

ከጦር መሳሪያ-ነፃ ትምህርት ቤት መመሪያዎች ላይ ጥሰት የፈጸመ አንድ ተማሪ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ህግ ስር የአካል-ጉዳት ያለበት ከሆነ፣ ዲስትሪክቱ ተግባራዊ ሊደረጉ በሚችሉ ሕጎች እና ደንቦች ስር በተደነገገው መሠረት የፌዴራል እና የግዛት መስፈርቶችን ያከብራል። እነዚህ ሕጎች እና ደንቦች አካል ጉዳተኛ ተማሪ የጦር መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት ይዞ ሲያመጣ የሚከተሏቸውን ልዩ አሰራሮች ይዘረዝራሉ። እነዚህ መመሪያዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ህግ መሠረት ማመልከቻቸው ፍቃድ እስካገኘ ድረስ በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ላይ ይተገበራሉ።

IV. በሌሎች የዲስትሪክቱ መመሪያዎች ላይ ያላቸው ተፈፃሚነት፡-

ሁሉም ሌሎች የዲስትሪክቱ የጦር መሣሪያ መመሪያዎች፣ የስነ ምግባር ፖሊሲዎች ወይም የጦር መሣሪያ መሳይ ቁሶች ላይ የተደነገጉ መመሪያዎች አሁን ባሉበት ወይም ከዚህ በኋላ በሚሻሻሉበት ጊዜ ተግባር ላይ ይውላሉ።

## የአውታረ-መረብ እና የበይነ-መረብ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም መመሪያዎች

በፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (FHSD) ውስጥ ለተማሪዎች፣ ለመምህራን፣ ለሰራተኞች፣ ለወላጅ(ጆች)/ለአሳዳጊ(ዎች) እና ለአስተዳዳሪዎች በይነ-መረብ ተደራሽነት እንዲሆን ተደርጋል። ተማሪዎች የ FHSD ቴሌግንኙነቶችን በዲስትሪክቱ መመሪያ 6320 ን በተከተለ መልኩ መጠቀም አለባቸው። ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት ፈጠራን የሚያበረታቱ ከሥርዓት-ትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎችን እና የምርምር ርዕሶችን እና ሀሳቦችን እንዲያገኙ ይፈቀድላቸዋል።

እንዴት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ግንኙነት መፍጠር እና በሕዝባዊም ሆነ በግል አውታረ-መረቦች ላይ የሚገኘውን የመረጃ ሀብት ማሰስ እንደሚቻል መማር በ 21ኛው ክፍለ ዘመን ለተማሪ ስኬት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ የመረጃ ትምህርት ክህሎቶች ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በክፍል መምህሩ ተቀባይነት ካገኙ፣ ተማሪዎች ለትምህርት ዓላማዎች የራሳቸውን ቴክኖሎጂ (ለምሳሌ፡- ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ አይፖዶች፣ አይፓዶች፣ የኤሌክትሮኒክ ማንበቢያዎች፣ የጭን ኮምፒውተሮች፣ ወዘተ.) ይዘው እንዲመጡ ይፈቀድላቸዋል።

ለደህንነት ዲስትሪክቱ ኬላ (firewall) እና ማጣሪያ (filtering) በመጠቀም CIPA (የሕፃናት የበይነ-መረብ ጥበቃ ህግን) መከበሩን ያረጋግጣል። ነገርግን፣ ተማሪዎች ምቾት የማይሰጣቸውን መረጃ ካገኙ ወዲያውኑ ለመምህራቸው ወይም ለሌላ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ማሳወቅ አለባቸው።

የሚከተሉት ተግባራት በዲስትሪክቱ አውታረ መረቦች ላይ ይፈቀዳሉ፡-

- የቴሌመገናኛ ዘዴዎችን ለትምህርት ዓላማዎች ብቻ ተጠቀም/ሚ
- ከሌሎች ጋር ክብር እና ትህትና በተሞላበት መንገድ ብቻ ተገናኝ/ኚ
- የሌሎችን የቅጂ መብት ህጎች እና የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችን አክብር/ሪ
- የግል ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ አድራሻ እና የይለፍ ቃል ግላዊነትን ይጠብቁ እንዲሁም የሌሎች ግላዊነትንም አክብር/ሪ

እነዚህ መመሪያዎች ተዘጋጅተው የቀረቡት ኃላፊነቶችዎን እንዲያውቁ ለመርዳት ነው። መመሪያዎቹ ተግባራዊ ካልተደረጉ የአውታረ-መረብ አስተዳዳሪው ወይም የተመደበው የ FHSD ተወካይ አውታረ መረብ/ኮምፒዩተር የመጠቀም መብቶችን ሊሰርዙ/ለገፍፉ ይችላሉ።

የሚከተሉት ተግባራት በዲስትሪክቱ አውታረ-መረቦች ላይ ክልከላ ተጥሎባቸዋል:-

- ሚስጥራዊ መረጃን ማጋራት
- የእርስዎን የይለፍ ቃል ለሌሎች አሳልፎ መስጠት
- የግል መረጃን በይነ-መረብ ማጋራት
- በማንኛውም መንገድ ሌሎችን መተንኮስ፣ መሳደብ ወይም መጉዳት
- የደህንነት ስርዓትን ጥሶ ለማለፍ/ለማቋረጥ ወይም ለመስበር መሞከር
- ወሲብ ነክ/ሕገ-ወጥ ይዘትን ፈልጎ ማግኘት
- ሶፍትዌርን በህገ-ወጥ መንገድ መገልበጥ
- የሌሎች ተማሪዎች አቃፊዎች፣ ማህደሮች ወይም ሰነዶችን ድንበር ጥሶ ማለፍ
- የሌሎችን ውሂብ/ማህደሮችን ለማውደም ወይም ለመጉዳት መሞከር
- አውታረ-መረቡን ለንግድ ዓላማዎች መጠቀም
- የብልግና ቋንቋን መጠቀም
- ስርአተ-ትምህርታዊ ያልሆኑ የበይነ-መረብ ጨዋታዎችን መጫዎት
- የቅጂ መብት ህጎችን መጣስ ወይም ኩረጃ
- ያልተፈቀዱ ድህረ-ገፆችን መጠቀም
- የዲስትሪክቱን አውታረ-መረብ ወይም ቴክኖሎጂ ማበላሸት
- ቫይረሶችን መጫን፣ ውሂብን መለወጥ ወይም የተከለከለ መረጃን መስረቅ

የአውታረ-መረብ እና የበይነ-መረብ አጠቃቀምን በተመለከተ የዲስትሪክቱ መመሪያ 6320 ን መጣስ ከሚከተሉት ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ፣ ነገርግን በዚህ ብቻ ያልተገደበ የቅጣት ውጤትን ያስከትላል:- 1) በአውታረ-መረቡ የመጠቀም ልዩ መብትን ማገድ ወይም መሰረዝ፤ 2) የበይነ-መረብ መጠቀም መብትን ማገድ ወይም መሰረዝ፤ 3) የኮምፒተር የመጠቀም መብትን ማገድ ወይም መሰረዝ፤ 4) ከትምህርት ቤት መታገድ፤ ወይም 5) መባረር።

እባክዎን ያስታውሱ:- ለልጅዎ/ለተማሪዎ የተናጠል የበይነ-መረብ መጠቀም መብትን ለመንፈግ ከፈለጉ፣ ተገቢውን የሚሞላ ቅፅ ለማግኘት እባክዎን ልጅዎ የሚማርበትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

## አካላዊ ቅጣት ክልክል ነው

የዲስትሪክቱ ፖሊሲ 2670 እንዲህ ይላል:- ለዲስትሪክቱ የተቀጠረ ወይም በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግል ማንኛውም ሰው በዲስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኝ ተማሪ ላይ አካላዊ ቅጣት አይፈፅምም ወይም እንዲፈፅም አይፈቀድለትም። የዲስትሪክቱ ሠራተኛ ራስን ለመከላከል፣ ስርዓትን ለማስከበር ወይም የሌሎች ሰዎችን ወይም የዲስትሪክቱን ንብረት ለመጠበቅ አስፈላጊ ከሆነ ለርዕሰ-መምህሩ/ተወካዩ አስቀድሞ ሳያሳውቅ በተማሪው ላይ በጥንቃቄ ምክንያታዊ የሆነ አካላዊ መግቻን ሊጠቀም ይችላል።

## የአውቶቡስ መመሪያዎች

የፍራንሲስ ሀውል አውቶቡስ አሽከርካሪዎች በዲስትሪክቱ አውቶቡሶች ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓት ያለው አካባቢን የመፍጠር ብሎም የማስጠበቅ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

- የሚከተሉት በዲስትሪክቱ አውቶቡሶች ላይ በሚጓዙበት ወቅት ከተማሪዎች የሚጠበቁ ነገሮች ዝርዝርን አካትቷል:-
- በተማሪው ስነ ምግባር ኮድ ውስጥ ያሉ ሁሉንም የሚጠበቁ ነገሮች ተከተል/ይ
- የአውቶቡስ ሹፌሩ የሚሰጠውን ሁሉንም መመሪያዎች ተከተል/ዪ
- ወደ አውቶቡሱ የፊት ለፊት ክፍል ፊትክን/ሽን አዙረክ ተቀመጥ/ጪ
- በተሰየሙ የአውቶቡስ መሳፈሪያ እና መውረጃ ላይ ብቻ ይሳፈሩ እንዲሁም ይውረዱ
- ሁሉንም የሰውነት ክፍሎችህን/ሽን እና ሁሉንም እቃዎችህን/ሽን አውቶቡሱ ውስጥ አቆዩ
- ሌሎችን (በቃልም ሆነ በአካል በሁለቱም) በአክብሮት ይያዙ
- አውቶቡሱን በአክብሮት ይያዙ (አካላዊ ጉዳት፣ ማቆሸሽ፣ እቃዎችን መወርወር፣ ምግብ መመገብ ወይም መጠጣት አይፈቀድም)
- በተመደብክበት/ሽበት አውቶቡስ ብቻ ተጓዝ/ዢ

ማስታወሻ፡- ሁሉም አውቶቡሶች በየትኛውም ወቅት በካሜራ ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚችሉ አስታውሱ።

ስርዓትን ለማስጠበቅ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመፍጠር የአውቶቡስ ሹፌሩ ማናቸውንም የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡-

- ከተማሪ ጋር ጉባኤ ማካሄድ
- ከርእሰ መምህር/ወኪል ጋር ጉባኤ ማካሄድ
- ተማሪዎች ህግጋትን እንዲያከብሩ ማዘዝ
- የአውቶቡስ መቀመጫዎች ለተማሪዎች መመደብ
- የአውቶቡስ ትኬት ማስጠንቀቂያዎችን መስጠት
- የአውቶቡስ ትኬቶችን መስጠት

የፍራንሲስ ሀውል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት (FHSD) አውቶቡሱ የመማሪያ ክፍል ቀጣይ ክፍል እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራል፤ ስለዚህ፣ አውቶቡስ ላይ የሚከሰት የስነ ምግባር ደምብ ጥሰት ቅጣት ያስከትላል። ቅጣቶቹም ከአውቶቡስ መታገድን ሊያጠቃልል ይችላል። ጥሰቱ ከባድ እና/ወይም የተማሪዎችን ጠቅላላ ደህንነትን አደጋ ላይ የጣለ ሲሆን፣ ጉዳዩ ወዲያውኑ ወደ ርዕሰ መምህሩ/ወኪሉ ይተላለፋል። ርዕሰ መምህሩ/ወኪሉ የመፈፀም/ካስፈለገ ተለዋጭ የቅጣት እቅድ የማጎልበት ነፃነት አለው። የቀጠናው የትራንስፖርት ዳይሬክተር እና የትራንስፖርት ደህንነት ሥራ አስኪያጅ ሲፈለግ ወይም አስፈላጊ እንደሆነ ሲታሰብ ከርዕሰ-መምህሩ/ተወካዩ ጋር ይገናኛሉ።

## የቃላት መፍቻ

**የተባለ/የተነገረ**

ያለማስረጃ፣ የተባለ/የተነገረ፣ የተፈፀመ ወይም የተገለፀ ህገወጥ ወይም ተፈላጊ የጥራት ደረጃ የሌለው።

**ጉልበተኝነት**

ጉልበተኝነት በትምህርት ምክር ቤት መመሪያ 2655 ላይ ሆን ተብሎ በግለሰብ ወይም በግለሰቦች ቡድን በተደጋጋሚ የተፈፀመ ወይም የመደገም እድሉ ከፍተኛ የሆነ ዛቻና ማስፈራሪያ፣ አስፈላጊ ያልሆነ ፀብ አጫሪ ባህሪ ወይም ትንኮሳ እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነ ተራ ተማሪን ለእራሱ ወይም ለእራሷ አካላዊ ደህንነት ወይም ንብረት እንዲሰጋ/ድትሰጋ የሚያደርግ፣ በማንኛውንም ተማሪ ላይ ያለልዩነት፣ በትምህርት አፈፃፀም፣ በመልካም አጋጣሚ አጠቃቀም፣ ወይም ጥቅማጥቅም ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳድር፣ ወይም የትምህርት ቤቱን አሰራር የሚያስተጓጉል ተግባር ነው ተብሎ ይተረጎማል። ጉልበተኝነት የምልክት ቋንቋን ወይም ቃላዊ፣ የሳይበር ጉልበተኝነትን፣ የኤሌክትሮኒክ፣ ወይም የፅሁፍ ግንኙነቶችን እና የጉልበተኝነት ተግባራትን ሪፖርት በሚያደርግ ላይ የሚወሰድ የትኛውም የበቀል ዛቻን ጨምሮ አካላዊ ጥቃትን ሊያጠቃልል ይችላል።

ዲስትሪክቱ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ፣ በትምህርት ሰዓት፣ በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረገ ተግባር ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተዛመደ አውድ ውስጥ ተማሪዎችን ከማንኛውም ዓይነት ጉልበተኝነት ወይም ማስፈራራት/ዛቻ በመከላከል ነፃ የትምህርት እና የሥራ አካባቢን ለማስጠበቅ ቁርጠኛ ነው። ማንኛውንም የሚከሰቱ የጉልበተኝነት አጋጣሚዎችን ተጠቂ ተማሪው እና/ወይም የእርሱ ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ለህንፃ አስተዳዳሪያው እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ።

ዲስትሪክቱ ተማሪዎች ጉልበተኝነትን በተመለከተ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያበረታታል። ተማሪዎች ተጎጂ ወይም ቆሞ ተመልካች ከሆኑ ማመልከት አለባቸው። ትምህርት ቤቶች ጉልበተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ አስተማማኝ መንገዶችን ለተማሪዎች ያሳውቃሉ። ጥቃት የደረሰባቸው ወይም የጉልበተኝነት ጥቃት ሲሰነዘር ቆመው የተመለከቱ ተማሪዎች አጋጣሚውን ወዲያውኑ ለአዋቂዎች ማሳወቅ አለባቸው። ልጁ ሪፖርት ማድረግ የማይመቸው ከሆነ ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጃቸው ላይ የተፈፀመውን ጉልበተኝነት ሪፖርት ለማድረግ ከርዕሰ-መምህሩ ጋር መወያየት አለባቸው። እያንዳንዱ ጉልበተኝነት ላይ የተጠናቀረ ዘገባ ይመረመራል። የ FHSD ድረ-ገፅ በዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ ላይ ደህንነት እና ጥበቃ በሚለው ስር ለወላጆች እና ለተማሪዎች የሚያገለግሉ ጉልበተኝነትን የሚመለከቱ ሀብቶች/ግብዓቶች አሉት።

**ጉባኤ**

ፊት ለፊት፣ በቪዲዮ ወይም በስልክ የሚደረግ ግንኙነት።

**የሳይበር ጉልበተኝነት**

የሳይበር ጉልበተኝነት በመመሪያ 2655 ላይ እንደተተረጎመው በስልክ፣ በገመድ አልባ ስልክ ወይም በሌላ ገመድ አልባ የመገናኛ መሣሪያ፣ ኮምፒተር ወይም የሬዲዮ መገናኛን ጨምሮ ነገር ግን በዚህ ብቻ ባልተገደበ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ አማካኝነት መልእክት፣ ጽሑፍ፣ ድምጽ ወይም ምስልን ጨምሮ ነገርግን በዚህ ብቻ ባልተገደበ የግንኙነት ማስተላለፍ ተብሎ ይተረጎማል። የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቱ የሚደረገው የትምህርት ቤቱን የቴክኖሎጂ ሀብቶች በመጠቀም ከሆነ፣ ከትምህርት አከባቢው ጋር በቂ ትስስር ካለ፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቱ ከተደረገ የተማሪውን የግል የቴክኖሎጂ ሀብቶች በመጠቀም በዲስትሪክቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በዲስትሪክቱ በሚሰጡ ተግባራት ላይ ከሆነ፤ በማንኛውም የዲስትሪክቱ ቅጥር ግቢ ወይም በዲስትሪክቱ ተግባራት ላይ የሚነሳ የሳይበር ጉልበተኝነት ሊከለከል እና ሊቀጣ ይችላል። በተጨማሪም፣ ከቅጥር ግቢ ውጭ በዲስትሪክቱ ተማሪዎች በሚሰጥ ትምህርት ላይ ቁሳዊ እና አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትሉ ከፍተኛ የስነ-ምግባር ጉድለት ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች ለቅጣት ተጋላጭ ይሆናሉ።

**ትንኮሳ/አድልዎ**

በግለሰቡ ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጎሳ፣ አካል ጉዳት፣ ኃይማኖት፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የታሰበ ጾታዊ ዝንባሌ ምክንያት ከሚደርስ ትንኮሳ-ነፃ የሆነ የመማር ማስተማር አካባቢን ማስጠበቅ የዲስትሪክቱ ፖሊሲ ነው። ዲስትሪክቱ በዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጎሳ፣ አካል ጉዳት፣ ኃይማኖት፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የታሰበ ጾታዊ ዝንባሌ ምክንያት ከሚደርስ ማናቸውንም እንዲሁም ሁሉንም ያካተተ ትንኮሳ ይከለክላል።

የትምህርት ቤት ስርዓቱ በዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ ጎሳ፣ አካል ጉዳት፣ ኃይማኖት፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የታሰበ ጾታዊ ዝንባሌ ምክንያት ከሚደርስ መደበኛም ወይም ኢ-መደበኛ፣ ቃላዊ ወይም የፅሁፍ አንዲሁም ሁሉንም የትንኮሳ ወይም የአድልዎ ቅሬታዎችን በፍጥነት ለመመርመር፣ ግለሰቦችን ከተጨማሪ ትንኮሳ ወይም አድልዎ ለመከላከል በፍጥነት ተገቢ እርምጃ ለመውሰድ፤ እና ትንኮሳ ወይም አድልዎ እንደተፈፀመ ከወሰነ፣ እንደተነኮሰ/እንዳዳላ፣ ማንኛውም ተማሪ፣ መምህር አስተዳዳሪ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሰራተኛን በፍጥነት እና በተገቢነት ለመቅጣት እና/ወይም ትንኮሳን ለማስቆም በምክንያታዊነት የተሰላ ሌላ ተገቢ እርምጃ ለመውሰድ ይሰራል።

**ተንኮል መስራት**

ተማሪ ላይ ተኮል መስራት በዲስትሪክቱ መመሪያ 2920 በግልጽ የተከለከለ ነው። ተንኮል መስራት ማለት አንድ ተማሪን ከትምህርት ቤት ጋር በሚዛመድ ተግባር ወይም በአትሌቲክስ ቡድን አባልነት ለማስተናገድ ዓላማዎች በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ንብረት ውጭ ሆን ተብሎ የሚደረግ ባህሪ ነው።   በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ባህሪዎችም የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰኑም ብልቶች፣ መቀመጫዎች ወይም ጡቶችን (የሴት ተማሪዎችን) ማጋለጥ ወይም መንካት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የውስጥ አልባሳትን መንካት፤ የአካላዊ ጉዳት ለማድረስ መዛት፤ እና አካላዊ ወይም አእምሯዊ ጉዳት ማድረስ ወይም ማዋረድን ያጠቃልላል፣ ነገርግን በዚህ ብቻ አይገደብም።

ይህንን ፖሊሲ ተላልፈው የተገኙ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት መታገድ/መባረር እና በጥፋቱ ክብደት ላይ ተመስርቶ ከድርጊቶች/የአትሌቲክስ ተሳትፎ መታገድ እና መባረር ሊከተል ይችላል።

**የተጋረጠ አደጋ**

የተወሰነ አደጋ፣ ወዲያው ሊከሰት የሚችል፣ እና የማይቀር፤ ቅርብ የሚገኝ እና አስጊ።

**ዛቻ/ማስፈራሪያ**

ዛቻ/ማስፈራሪያ ሆን ተብሎ የሚከናወን ባህሪ ሲሆን የተለመዱ ስሜታዊ/ሥነ ልቦናዊ ምላሾችን ባለው መደበኛ ሰው ላይ በደል ወይም ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ እንዲፈራ የሚያደርግ ክስተት ነው። ባህሪው ኃይለኛ በመሆኑ ያደርሳል ተብሎ የተነገረውን ፍራቻ እንዲፈጥር ወይም ተጎጂው በትክክል መፍራቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም።

**ታማኝነት**

ማንኛውም ዓይነት ስርቆት ወይም ውሸት፣ በቃል ወይም በጽሑፍ የሚፈፀም፣ ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ጨምሮ።

**የመኪና ማቆሚያ ፈቃዶች**

በእያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ውስን በመሆኑ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መኪና ይዘው እንዲመጡ የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። የተማሪ መኪኖችን በሚመለከት ፍቃድ ለማግኘት እና ለሌሎች ደንቦች የብቁነት መስፈርቶችን በተገቢው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ አማካኝነት ይዘጋጃሉ። የህግ ጥሰቶች የመኪና ማቆሚያ ቦታ የማግኘት መብቶችን ሊያስነፍጉ ይችላሉ።

**ይዞ መገኘት**

ተማሪው ላይ ወይም በእቃ መቆለፊያ ሳጥን ውስጥ፣ በመኪና/ተሽከርካሪ ውስጥ (በዲስትሪክቱ ንብረት ላይ የቆመ ከሆነ)፣ በቦርሳ፣ በእጅ ቦርሳ ወይም በሌላ ዕቃ መያዣ ውስጥ ቁስ ይዞ መገኘት።

**ህጋዊ ጥበቃ የሚደረግላቸው (ትንኮሳ)**

ጾታ፣ ዘር፣ ብሔር፣ የዘር ሐረግ፣ እምነት፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ወላጅነት፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ መለያ፣ ጾታን ጨምሮ በፌዴራል፣ በግዛት ወይም በአከባቢው ህግ፣ ደንብ ወይም ድንጋጌ በግልጽ የተገለጸ እና ጥበቃ የሚደረግለት ማንኛውም ሁኔታ አገላለጽ፣ ወይም አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ስሜታዊ ወይም የመማር እክል።

**መሸመት/መግዛት**

በአደንዛዥ ዕፅ ምትክ ገንዘብ ወይም ሌላ ተመጣጣኝ ግምት ያለው ነገር መስጠት፣ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ምትክ በሌላ ቀን ገንዘብ እከፍላለሁ ወይም ሌላ ተመጣጣኝ ግምት ያለው ነገር እሰጣለሁ ብሎ ቃል መግባት።

**መመለስ**

የተሰረቁ ወይም የተበላሹ ዕቃ(ዎችን) መተካት ወይም በካሳ መልክ ወይም በአገልግሎት ልክ ተመጣጣኝ የሆነ የገበያ ዋጋን ማቅረብ።

**ከባድ የአካል ጉዳት**

ከባድ የአካል ጉዳት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያስከትል የአካል ጉዳት ዓይነት ነው።

- ጉልህ ለሆነ የሞት አደጋ ስጋትን የሚያጋልጥ
- ቋሚ የአካል ብልሽት ወይም ጉድለት የሚያስከትል
- ኮማ ውስጥ የሚያስገባ
- ከባድ ህመም የሚያስከትል ቋሚ ወይም ለረዥም ጊዜ የሚከሰት ሁኔታ
- በማንኛውም የሰውነት ክፍል ላይ ቋሚ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ መሳንን ወይም የአካል ጉድለትን የሚያስከትል።
- ሆስፒታል እንዲገቡ የሚያስገድድ

ከባድ የአካል ጉዳት፣ ይህም የተሰነጠቁ ወይም የተሰበሩ አጥንቶችን (አፍንጫን ጨምሮ) እንዲሁም መናጋትን ያጠቃልላል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም። ከባድ የአካል ጉዳት የበለዙ አይኖችን፣ እብጠቶችን፣ በፋፋቅ/መጋጋጦችን ወይም ሰንበሮችን አያካትትም።

**ከባድ ማስፈራሪያ**

ቃል አልባ ጥቃት/ማስፈራራትን፣ የቃል መግለጫዎች ወይም የጽሁፍ መግለጫዎችን ጨምሮ አንድን ሰው ምክንያታዊ በሆነ የአካል ጉዳት ስጋት ውስጥ የሚከት ምግባር ላይ መሳተፍ ማለት ነው።

**ወሲብ ነክ የፅሑፍ መልዕክት**

ልቅ የወሲብ ፎቶግራፎችን ወይም መልዕክቶችን በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ በኩል መላክ።

**ወሲባዊ ንክኪ**

የአንድን ሰው የፆታ ግንኙነት ፍላጎትን ለመቀስቀስ ወይም ለማርካት በማሰብ ወይም ለማጥቃት፣ ለማዋረድ ወይም ዝቅ ለማድረግ በማሰብ በቀጥታም ሆነ በአልባሳት ላይ ሌላ ሰው ሰውነትን እንዲነካ ማድረግ።

**መስረቅ/ስርቆት**

ያለባለቤቱ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ባለቤቱ እንዳይጠቀመው ለማገድ አስቦ (በስርቆት ወንጀሎች ስር) የሌላን ሰው ወይም ተቋሚ ንብረትን መውሰድ ወይም ለመውሰድ መሞከር።

**ጉልህ የሆነ ማስፈራሪያ**

ተጠቂዎችን ከጉዳት ለመከላከል እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ ዓላማ ያለው ማስፈራሪያ።

**ማሾፍ**

የተጠቂው ሞራልን ለመንካት ወይም ለማስቆጣት እንዲሁም ሳያስብ የአጸፋዊ ባህሪያትን እንዲሰጥ ለማበረታታት የታሰቡ የአሽሙር መግለጫዎች፣ የሰውነት ምልክቶች ወይም ስድቦች።

**የአሻንጉሊት ጠመንጃ/መሳሪያ**

ሽጉጦችን እና ሌሎች ጠመንጃዎችን ጨምሮ እውነተኛ የጦር መሳሪያዎችን የሚመስሉ መጫወቻዎች፣ ልጆችን ለማዝናናት እንደ ዕቃ ሆነው ሊገለግሏቸው  ታስበው የተዘጋጁ ሲሆን አደገኛ አይደሉም።

**ጊዜያዊ ማስፈራሪያ**

የቀልድ፣ ሽንገላ ንግግሮች፣ የቁጣ ወይም የብስጭት መግለጫ የያዘ ማስፈራሪያ በቀላሉ ሊፈታ የሚችል እና ጉዳት ለማድረስ ዓላማ የሌለው። ጉልህ ጉዳት ለማድረስ ያላለመ

**መተላለፍ**

ታግዶ ወይም ተባርሮ እያለ ያለ ፈቃድ በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ መገኘት፤ ሰብሮ መግባትንም ያካትታል። ወይም የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ግለሰቡን ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢው ለቅቆ እንዲወጣ ከጠየቀው በኋላ በት/ቤት ንብረት ውስጥ መቆየት። የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሕግ አስከባሪ አካላትን በመጥራት ተማሪውን፣ ወላጅን/አሳዳጊውን፣ ደጋፊውን ወይም ጎብኚውን በመተላለፍ ክስ እንዲከሰሱ ይጠይቃል።

**አለመተባበር/የህግ ጥሰት**

ተማሪው የትምህርት ቤት ህጎችን ወይም የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች ወይም የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች መመሪያዎችን ሳይከተል ሲቀር በትምህርት ቤቱ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድርበት ጊዜ ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆን ሊከሰት ይችላል፣ ለምሳሌ ግጭት ባለበት ቦታ መቆየት ወይም ባህሪውን እንዲያቆም ከተነገረው በኋላ ሁከት መፍጠር፣ ወይም ሌሎች የምላሽ ስልቶች መጥፎ ባህሪውን ለማሻሻል ተግባራዊ ተደርገው ካልተሳኩ ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች ተደጋጋሚ አለመታዘዝ ሊከሰት ይችላል። በሚከተሉት ጊዜዎች የህግ ጥሰት አይከሰትም:-

- ተማሪው በትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በጎ ፈቃደኞች የሚሰጠውን መመሪያ በአግባቡ ሳያውቅ/ሳይረዳ ሲቀር (ማለትም፣ ጫጫታ በበዛበት ክፍል ውስጥ፣ የመስማት ችግር ወይም ሌላ አካል ጉዳተኝነት ካለበት፣ የቋንቋ ገደቦች፣ ወዘተ.)።
- ተማሪ ከትምህርት ቤት ሲያረፍድ፤
- ተማሪው የቤት ስራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ሳይችል ሲቀር

**በተፅዕኖ ስር መውደቅ**

አንድ ተራ መደበኛ ሰው በሚሠራበት መንገድ በአንድ ሰው የመሥራት አቅም ላይ እንቅፋት የሚፈጥር የአልኮል ወይም አደገኛ ዕጾች አጠቃቀም።

**ቶሎ የሚለወጥ**

በፍጥነት እና ሳይጠረጠር ድንገት የሚለወጥ፣ በተለይም በአሉታዊ መንገድ መባባስ።

**የጦር መሳሪያ (መሰሎች እና ጥይቶችን ጨምሮ)**

የጦር መሣሪያ፣ በተምሳሌትነት እና ያለገደብ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ነው:-

- <u>የጦር መሣሪያ</u>: በፌዴራል ህግ 18 U.S.C. 921 ውስጥ እንደተተረጎመው የጦር መሣሪያ። ምሳሌዎች የእጅ ሽጉጦችን፣ ጠመንጃዎችን፣ ተተኳሽ መሳሪያ (shotguns) እና ቦምቦችን ያካትታሉ። ለተሟላ ትርጓሜዎች የፌዴራል ህግን ይመልከቱ።
- <u>ሌሎች ሽጉጦች</u>: ከጦር መሣሪያ ውጭ ሌላ ጥይት የሚመስል ማንኛውንም ቁስ ጨምሮ ቀለህ የገባበት ወይም ያልገባበት፣ ሊሠራ የሚችል ወይም ሊሠራ የማይችል ማንኛውም ዓይነት ሹጉጥ። ይህ የጥይት ሽጉጥ፣ የቀለም ኳስ ሽጉጥ፣ አንቂ ሽጉጥ፣ የቴዘር ሽጉጥ፣ BB ሽጉጥ፣ የአብሪ ጥይት ሽጉጥ፣ የሚስማር ሽጉጥ እና የአየር ሽጉጥ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የማይገደብን ያጠቃልላል።

- <u>ሌሎች የጦር መሣሪያዎች</u>: ከጦር መሳሪያ ወይም ከሌላ ጠመንጃ በስተቀር፣ በአካል ላይ ችግር እና/ወይም ጉዳት የሚያስከትል ወይም እንዲያስከትል ታሳቢ ሊደረግ የሚችል በአስፈሪ ሁኔታ ጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም ቁስ ወይም እቃ። ይህ ታጣፊ ቢላዋ፣ የአደን ቢላዋ፣ ኮከብ ቢላዋ፣ ምላጭ (ቀጥ ያለ ወይም ተመላሽ ምላጭን ጨምሮ)፣ የነሐስ አንጓዎች፣ የሳጥን መቁረጫ፣ ባለገመድ ቆመጥ፣ ባለመንጠቆ ዱንት፣ ባለመንጠቆ የእጅ አምባር፣ ማንኛውም የባለከብ መንጠቆ ቆመጥ ዝርያ፣ የአስለቃሽ ጋዝ መሣሪያ ወይም በርበሬ የሚረጭ ምርትን ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የማይገደብን ያጠቃልላል።

የጦር መሳሪያን የሚተረጉም የሚዞሪ ግዛት ህግ በሚከተለው ማስፈንጠሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል:
[Missouri Statute](#)